# ኢየሩሳሌምን
# ዐወቁ

www.ethiopianorthodox.org

በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ
በ፴፪ኛው ዘመነ መንግሥት ይህ መጽሐፍ ብርሃንና ሰላም
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ደራሲው ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ አርቶዶክሳዊ ሊቀ ጳጳስ
ያለደራሲው ፈቃድ መልሶ ማሳተም
በሕግ የተከለከለ ነው ።



የኢትዮጵያ መሪ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አፄ ኃይለ ሥላሴ በልጅነት ።

አምላክ የመረጠው ፡ ለኢትዮጵያ ዕድገት
ሕፃኑ ተፈሪን እዩት ሲመለከት
ወሰኑን ለማቅናት ፡ ባሕሩንም ለመክፈት ።

www.ethiopianorthodox.org

ግንቦት ፲፯ ቀን ፲፱፻፷፫ ዓ. ም.

# የግርማዊነታቸው ታሪክ መግቢያ ።

## ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ጃንሆይ ፤

ከዚህ ቀጥዬ የምጽፋቸው ቃላት በዓይን ያየኋቸውን ፤ በገሮዬም የሰማኋቸውን ፤ በአእምሮዬም የተረዳኋቸውን እንጂ እንዲያው እንደ ሰው ልማድ ግርማዊነትዎን በከንቱ ለማሞገስ ለከንቱ ውዳሴ የተጻፉ አለመሆናቸውን አስቀድሜ እመሰክራለሁ ።

ግርማዊ ሆይ ፤ ስምን መልአክ ያወጣል ይባላል ፤ « ስሙ ይመርሖ ኀበ ግብሩም» ይላሉ ። የዓለም ስምዎ ተፈሪ ፤ የፈረስ ስምዎ ጠቅል ፤ የሃይማኖት ስምዎም ኃይለ ሥላሴ ተብለዋል ።

ይህም ስያሜ ከእግዚአብሔር የተነገረ ትንቢታዊ ስም መሆኑን አስረዳለሁ።

፩ኛ/ ተፈሪ ፤ ቃልዎ ተደማጭ ፣ ግርማዎም አስደንጋጭ ለመሆኑ ከልዑል እግዚአብሔር ለተሰጠዎት ግርማና ሞገስ የተነገረ ትንቢታዊ ቃል ነው ።

፪ኛ/ ጠቅል ፤ ኢትዮጵያን ባንድ ሕገ መንግሥት ጠቅልለው ለመምራትዎና መላ አፍሪካንም ባንድ አዳራሽ ሰብስበው የአፍሪካን አንድነት መሥርተው ባንድ ሕግ ለማዋሐድዎ የተነገረ ትንቢታዊ ቃል ሲሆን ።

፫ኛ/ ኃይለ ሥላሴ ፤ ይህም ስያሜ በሥጋዊ ኃይል ጥሼ ልንገሥ ሳይሉ በሥላሴ ኃይል በልዩ ጥበቡም በሕዝብ ተመርጠው ከሐረር ተጠርተው እግዚአብሔር ለፍጥረቶቹ ለሚሠራው ሥራ ሠራተኛ ይሆኑ ዘንድ የተነገረልዎ ትንቢታዊ ቃል መሆኑን በተረዳሁት መጠን በእግዚአብሔር መንፈስ እገልጻለሁ ።

## ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጃንሆይ ፤

ከዚህ በላይ ባለው መሥመር በሥላሴ ኃይል የተመረጡበት ጠቅላላ ዕድልዎን ስላነሣሁም መላ ዓለምን ያስደነቀው ጠቅላላው ታሪክዎን ለታሪክ ጸሐፊዎች ትቼ በዚች ለኢትዮጵያ ወጣት ታሪክ መርማሪዎች በሀገር ቅድስት በኢየሩሳሌም ለኢትዮጵያ ያላትን የሥጋዊና መንፈሳዊም መሠረተ ተዘምዶና አባቶቻቸው ያቆዩት አፅመ ርስት ቅርሳቸውንም ያውቁ ዘንድ ባለኝ ሐሳብ «ኢየሩሳሌምን ዕወቁ» በሚል ስያሜ ባዘጋጀሁት ጽሑፌ መቅድም ገጽ ፤ ግርማዊ ለኢትዮጵያ ሕዝብዎ በመንፈሳዊ ዕድገቱ የዋሉለት ድንቅ የሆነ ውለታዎን ብቻ እንደሚከተለው እገልጻለሁ ።

www.ethiopianorthodox.org

አንደኛ ፤ በወጣቱ ዕድሜዎ ወደ ሀገር ቅድስት ወደ ኢየሩሳሌም ሔደው ከላይ በተሰጠዎ መንፈሳዊ ቅንዓት መካናት ቅዱሳትን ሲጐበኙ በኢትዮጵያ ውያን ዜጎችዎ ላይ የተመለከቱትን ኑሮ ለማሻሻል ።

ሀ. ከግሪክ ኦርቶዶክስ ፓትሪያርክ ከአባ ድምያኖስ ጋራ ስለማኅበሮችዎ ኑሮ ያደረጉትን ንግግርና ጥልቅ ስሜትዎን ።

ለ. በኢየሩሳሌም ገዳምዎ በዚያን ጊዜ የተገኘነውን መምህርና የማኅበሩን ቃል በትዕግሥት አዳምጠው ይህን ነገር ገና ከአዲስ አበባ ስነሣ አስቤዋለሁ ፣ አሁንም በዚህ ሰሞን ወደ ምድረ ግብፅ ለመውረድ አስቤአለሁና ነገሩ በሰላም እንዲጨረስ አደርጋለሁ ሲሉ በማረጋጋት የሰጡንን ተስፋ ፤

ሐ. በዚያን ጊዜ ለነበሩት የግብፅ ጳጳስ ለአቡነ ጢሞቴዎስ የጻፉት ታሪካዊ የሆነ መልእክትና ፤ ወደ ግብፅ ወርደው ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን አባሎች የተነገረዎትን መልስ ሰምተው እንደወጣት የመኩራት ፤ እንደ ባለሥልጣንም የመገረም ጠባይ ሳይሰማዎ በረጋው ትዕግሥት ሆነው «እንኳን እኔ ራሴ መጥቼና መላክተኛም ብንልክ በማክበር ተቀብለው ደስ አሰኝተው የሚመልሱት ይመስለን ነበር እንጂ በአባቶችና በልጆች መካከል ይህን የመሰለ ነገር የሚሆን አይመስለንም ነበር እያሉ ለመኳንንቶቻቸው ነገሩዋቸው» ያለውን የደስታና ክብርን ቃል መሠረት በማድረግ ፤ ቀጥሎም በሕይወቱ ዘመን ሁሉ የተመለከትኩትን ፤ ግርማዊነትዎ በታላቅ ትግል ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዕድገት ከሥር እስከ ጫፍ ያደረሱዋቸውን መዓርጋት በመዘርዘር ፤

ሀ. በ፲፱፻፳፩ ዓ. ም. ከኢትዮጵያ ሊቃውንት ለጳጳስነት መዓርግ ማብቃትዎን ፤

ለ. ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳሳት አሹመው ጳጳሳት እንዲሾሙ አድርገው ፣ አባቶች ተለምነው አይሆንም ያሉትን የዴር ሡልጣንን ርስት በሕግ እንዲመለስ ያደረጉበትን ፍልስፍናዎን ፤

ሐ. ፲፱፻፶፩ ዓ. ም. ወደ ግብፅ ወርደው ኢትዮጵያዊ ፓትሪያርክን ማሾምዎና ፤

መ. ፍጻሜ መዓርጉንም ፣ ኢትዮጵያዊ ፓትሪያርክ ባገር ውስጥ ተመርጦ ባገር ውስጥ ሥርዓተ ሢመቱ እንዲፈጸም ባወጁት የነፃነት አዋጅዎ ኢትዮጵያውያንን ብቻ ያይደለ መላ ዓለምን ባስደነቀው አኳኋን ፣ የመላው ዓለም አብያተ ክርስቲያናት ፓትሪያርኮችና ሊቃውንት ተካፋይ በሆኑት በኢትዮጵያዊ ሥርዓተ ጸሎትና ቅዳሴ ፣ ግንቦት ፩ ቀን ሢመተ ፓትሪያርክን በታላቅ ክብር



አክብረው ፣ የፈጸሙትን ዘመን የማይሽረውን ታሪክዎን በመቅድሙ ለተከታይ ትውልድ እንዲቆይ አዘጋጆቼ የድካምዎን ፍጻሜ አስረድቼ ጽፌአለሁ ።

ሠ. በኢየሩሳሌም ላለው የኢትዮጵያ አፅመ ርስት አሁን ለተያዘው ለዴር ሡልጣን ጉዳይና ወደፊትም ወደ ቅዱሱ መቃብር ወደ ጎልጎታ ቤተ ክርስቲያን ለመግባት የሚያስችሉ ማስረጃዎች ከነፎቶ ኮፒው በዓረብና በእንግሊዝ አሳትሜ ትርጕሙን በራሳችን ቋንቋ ባማርኛ አዘጋጅቼ ለሰማንያኛው በዓለ ልደትዎ መታሰቢያ ሆኖ ይታተም ዘንድ እየተመኘሁ ለታላቁ ታሪካዊ ግርማዊነትዎ አቀርባለሁ ።

የሐሳብ አገልጋይዎ አባ ፊልጶስ

www.ethiopianorthodox.org



የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት አልጋ ወራሽ
ልዑል መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ።

www.ethiopianorthodox.org

መቅድም ።

# «ኢየሩሳሌምን ዕወቁ»

ይህ «ኢየሩሳሌምን ዕወቁ» የተባለ መጽሐፍ የኢትዮጵያ ሕዝብ በኢየሩሳሌም ላይ ያለውን በጣም ደስ የሚያሰኘውን መንፈሳዊ ታሪኩንና የእምነቱ ምልክት የሆኑት ቅዱሳት መካናት የሚገኙትን የሃይማኖት ቅርስ አፅመ ርስቶቹንም በማወቅ ይጠቀምበት ዘንድ ሁለተኛም ስለ ዴር ሡልጣን ገዳም ርስትነት ከግብፆች ጋር የተደረገውን የርስት ክርክርንና ሙግትን ፍጻሜ ለማስረዳት ከአባ ፊልጶስ በእግዚአብሔር ጸጋ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ሊቀ ጳጳስ ተጻፈ ።

ኢየሩሳሌም እንደ ኤሮፓ አቈጣጠር በ፲፱፻፷፪ ዓ. ም. በ፲፫፻፹፪ ሂጅራ ተጻፈ ።

፩/ ይህን መጽሐፍ «ኢየሩሳሌምን ዕወቁ» በሚል አርእስት የሰየምኩት ፤

አንደኛ ፤ የኢትዮጵያ ሰው መጽሐፉን አንብቦ ኢየሩሳሌም በብሉይ ኪዳን ሀገረ ሰላም የምትባልበትን ጥንተ ታሪኳን ለማስረዳት ።

ሁለተኛ ፤ በጌታችን በኢየሱስ ደም ተቀድሳ ሀገር ቅድስት መባልዋን ለማሳወቅ ፤

ሦስተኛ ፤ ይህች የታሪክ ከበርቴ የሆነችው ኢየሩሳሌም ከኢትዮጵያ ጋር እንዴት ያለ ግንኙነት እንዳላትና ለኢትዮጵያ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ በቀደሳቸው በቅዱሳት መካናትም የሃይማኖት ቀደምትነትና የርስት መብት ይዞታ እንዳላት እንድታውቁ ።

አራተኛ ፤ ዛሬም በዚች በቅድስት ሀገር የኢትዮጵያን ማኅበርና አፅመ ርስቱም በምን አኳኋን እንደሚገኝ የኢትዮጵያ ሰው ሁሉ ይህን ታሪካዊ የሆነውን መጽሐፍ በመመልከት በንብረቱና በማኅበሮቹ ላይ የተፈጸመውን የግፍ ሥራና አጥቂነትም ተግባር በማወቅ እንዲጠቀምበት ነው ።

፪/ ኢየሩሳሌም ለኢትዮጵያ ጥንተ ሕገ መንግሥትና ጥንተ ሃይማኖትም እንደሆነች ለማወቅ ትችሉ ዘንድ ታሪኩን በማስተዋል ተመልከቱ ፤ ለሰው ልጅ እርሱው ራሱ ማንነቱን በሥራና በቃሉም ካላወቀና ካላሳወቀ በቀር ማንም ሊያውቀውና ሊያውቅለትም አይችልምና ታሪካችንን መርምረን ዕድላችንን እኛው ራሳችን እናስከብረው ፤ ታሪካችንንም እኛው ራሳችን እንግለጠው።

ሰው ራሱን ሳያውቅና ሳይታወቅ የሌላውን አውቃለሁ ቢል ላዋቂዎች ተረት ይሆናል የራሱን አያውቅ መባል ታላቅ ስድብ ነውና ።

www.ethiopianorthodox.org

፫/ ማስረጃ ስለ አብርሃምና መልከ ጼዴቅ ለወጣቶች ፤

ወጣቶች ሆይ ! ፍቁረ እግዚአብሔር የመባልን ዕድል የወረሰው አብርሃም ካገርህ ወጥተህ ከወገኖችህ ተለይተህ እኔ ወደ ማሳይህ ምድር ና ተብሎ ከእግዚአብሔር የተጠራው አብርሃም ከአገሬ ወጥቼ ከወገኖቼ ተለይቼ ወዴት እደርሳለሁ ? ሳይል የእግዚአብሔርን ቃል አምኖ ካገሩ ከካራን ወጥቶ ዛሬ ኬብሮን ወይም ከሊል በመባል ወደ ታወቀችው አገር ወደ ከነዓን ምድር ተዛውሮ የሳሌም ንጉሥ የልዑል እግዚአብሔር ካህን በመባል ታውቆ ብቸኛው መልከ ጼዴቅ ወደሚኖርባት ሀገረ ሰላም ተብላ መልከ ጼዴቅን ንጉሠ ሰላም ወደ አሰኘችው ወደ ኢየሩሳሌም እንደገባና ከዚህም ከደገኛው ካህን ተገናኝቶ ካለው ሀብት አሥራት እንዳበረከተውና መልከ ጼዴቅም በረከቱን በሥርዓተ ካህን ተቀብሎ አብርሃምን እንደ ባረከው ለሐዲስ ኪዳን ቍርባን ምሳሌ የሆነ የወይን ጠጅና ኅብስትም ( እንጀራ ) እንዳቀረበለት መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል ። ዘፍ. ፲፬፡፲፯-፳።

፬/ የዚህም የመልከ ጼዴቅን ደግነት ዳዊት በመዝሙሩ «ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ ከሆድ ወለድኩህ ፤ እንደ መልከ ጼዴቅ ሥርዓት አንተ ለዘለዓለም ካህን ነህ» ብሎ «እግዚአብሔር ማለ ፡ አይጸጸትምም» በማለቱ ለእግዚአብሔር ልጅ ለኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ አድርጎ በተናገረው ትንቢት ገልጾታል ። መዝሙር ፩፻፱.፫ ፡ ፬ ።

፭/ ቅዱስ ጳውሎስም እንደዚሁ «የስሙም ትርጓሜ በመጀመሪያ የጽድቅ ንጉሥ ነው ፤ ኋላም ደግሞ የሳሌም ንጉሥ ማለት የሰላም ንጉሥ ነው ፤ አባትና እናት የትውልድም ቍጥር የለውም ፤ ለዘመኑም ጥንት (መነሻ) ለሕይወቱም ፍጻሜ የለውም ፤ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል» ብሎ ከላይ በነቢዩ የተነገረውን ትንቢት አብራርቶ ጽፎለታል ፤ ዕብ. ፯ ፡ ፩-፫ ።

፮/ ከአበው ታሪክም መልከ ጼዴቅን ከማየ አይኅ በኋላ የኖኅ ልጅ ሴም አዕመ አዳምን አስጠብቆ በማዕከለ ምድር በኢየሩሳሌም ዋሻ ውስጥ አስቀምጦት አዕመ አዳምን እንደ ታቦት አድርጎ ለእግዚአብሔር ጸሎትና መሥዋዕትም እያቀረበ ሙሴ ጽላትና ሕገ ኦሪትን ከመቀበሉ አስቀድሞ እግዚአብሔርን ያገለግል ነበር ፤ እያሉ ለክህነትና ለታቦት ጥንተ መሠረት አድርገው የሚተርኩ ይገኛሉ ። ሆኖም አገረ ሰላምን ስንሻ ስሙን ካነሳን ዘንድ ታሪኩንም ለመግለጽ ያህል ነው እንጂ ፤ እኔ የተነሣሁት ለኢትዮጵያ ከኢየሩሳሌም ጋር ከጥንትም ጀምሮ በብሉይና በሐዲስም ያላትን ተዘምዶ ለማስረዳት ነውና የመልከ ጼዴቅን ሐተታ በዚህ አቁሜ የተነሣሁበትን ታሪክ እቀጥላለሁ ።

፯/ «በሰማይ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን ፤ ሰላምም በምድር ፤ ለሰውም በጎ ፈቃድ» ብለው መላእክት የልደቱ ዕለት እንዳበሠሩ ንጉሠ ሰላም ኢየሱስ



ክርስቶስ በቤተ ልሔም በሰው ሥጋ በተወለደ ጊዜም እግዚአብሔር አብ አንድ ልጁን ልኮ ፍጥረቱን ሁሉ በታረቀው ጊዜ የዕርቅና የሰላም አዋጅ የተነገረባት የሰላም መግለጫ ምድር በመሆኗ ኢየሩሳሌም በሐዲስ ኪዳንም ሀገረ ሰላም ተብላለች ።

## ሁለተኛ ስለ ኢትዮጵያ ነገሥታት ታላቅ ዝና ።

፩/ ለኢትዮጵያ በሀገር ቅድስት በኢየሩሳሌም ያላት ታሪክ በሥጋዊና በመንፈሳዊም የተጣመረ ድርብ ታሪክ በመሆኑ ኢትዮጵያን በጣም የሚያኮራት ነው ። ይኸውም ጥሩ ታሪክ ኢትዮጵያ ያፈራችው እጅግ ስመ ጥሩ በሆኑት ብልሆች ነገሥታቷ ዕውቀትና አስተዋይነትም ነው ።

፪/ ለዚህም አስተዋይነት መገኛው ከእግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ ከሰው ብልጠት እንዳይደለ በነቢዩ በዳዊት «ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች» ተብሎ አስቀድሞ የተነገረላት ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ኢትዮጵያዊት ንግሥት ያደረገችው ጉዞ የሚያስረዳ ነው ።

፫/ «የሳባ ንግሥት በእግዚአብሔር የወጣለትን የሰሎሞንን ዝና በሰማች ጊዜ በዕንቈቅልሽ ትፈትነው ዘንድ መጣች» በማለት ብሉይ ኪዳን እንደገለጸው ይህችው ዝነኛዋ የኢትዮጵያ ንግሥት በንጽሕና ፡ በድንግልና ተጠብቃ የዓለምን ታሪክ ስትመረምር የሰሎሞንን ብልህነት በሰማች ጊዜ በወሬ የሰማችውን ሥጋዊና መንፈሳዊ ጥበቡን በዓይን ዓይታ ለመረዳት ስትል እንደዛሬ ዘመን የባሕርና የአየር ጐዳና ባልተከፈተበት ዘመን በሴት አቅሟ ከአክሱም እስከ ኢየሩሳሌም ባደረገችው በረጂም ጉዞ ከሰሎሞን ተገናኝታ የተመኘችውን ሥጋዊና መንፈሳዊ ጥበቡን ራሷ ለመረዳት ቻለች ።

፬/ ለእግዚአብሔር ትንሽ ነገር ሲለምኑት ታላቅ ስጦታ መስጠት የቸርነት ባሕርዩ እንደመሆኑም ያላሰበችውንም ስጦታ ሰጣት ። ይኸውም ስጦታ የምድር ነገዶች ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ የሚለው የተስፋ ትንቢት ከተነገረለት ከአብርሃም ዘር ከወረደው የይሁዳ ነገድ ከሆነ ከሰሎሞን በዙፋንዋ የሚተካ ቀዳማዊ ምኒልክን ጸንሳ ፤ የእግዚአብሔርን እምነት አጥንታ በመመለሷ «ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ» የሚለውን ለኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ ታላቅ የባለተስፋ ዘር ያደረገውን ዓላማ የትውልድ ሐረግና የእምነትን መሠረት አግኝታ ተመልሳለች ። ፩ኛ/ ነገ ፲ ፡ ፩-፲፫ ።

፭/ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በስብከቱ የሰሎሞንን ጥበብ ለመረዳት ባደረገችው ጉዞ እንዳመሰገናት ሐዲስ ኪዳን ይነግረናል ። ሉቃ ፲፩ ፡ ፴፩ ።

፮/ ከዚህ መሥመር በላይ ንግሥተ አዜብ የፈጸመችው ልባምነት በጌታችን ቃል እንደ ተመሰገነች በቅዱስ ወንጌል ሲነገር ይኖራል ።

www.ethiopianorthodox.org

፯/ በተከታይዋ በንግሥት ሕንደኬ ዘመነ መንግሥትም በሐዲስ ኪዳን የተፈጸመውም ታሪክ እንደዚሁ ኢትዮጵያን በጣም የሚያኮራ ነው ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ ተአምራት በማሳየት ፫ ዓመት ከ፫ ወር ያስተማረው ሕዝብ መድኃኒቱን ሰቅሎ በስሙ ያመኑትንም በማሳደድ ላይ ሳለ ፤ የኢትዮጵያዊት ንግሥት የሕንደኬ መላክተኛ ኢትዮጵያዊ ሰው በብሉይ ኪዳን እምነት ሕግ በዓሉን አክብሮ ሲመለስ በሠረገላው ተቀምጦ እንደ በግ ወደ መታረድ ተነዳ ፤ የበግ ጠቦትም በሸላቹ ፊት ዝም እንደሚል አፉን አልከፈተም ። የሚለውን የኢሳይያስን ትንቢት እያነበበ ሲጓዝ ሳለ ፤ ሐዋርያው ፊልጶስ ከእግዚአብሔር ታዝዞ ደረሰበትና በውኑ የምታነበውን ታስተውለዋለህን ? ቢለው የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል አለው ፤ ወዲያው ፊልጶስን በሠረገላው አስቀመጠውና እባክህ ነቢዩ ይህን ስለማን ይናገራል ስለ ራሱ ነውን ? ወይም ስለ ሌላ ? አለው ፤ ፊልጶስም ከዚህ መጽሐፍ ጀምሮ ስለ ኢየሱስ ወንጌልን ሰበከለት ፤ ሲጓዝም ውኃ ካለበት ደረሱና ኢትዮጵያዊው ሰው እነሆ ውኃ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ አለን ? ቢለው ሐዋርያው በፍጹም ልብህ ብታምን ተፈቅዶልኻል ቢለው ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ ብሎ ሠረገላው እንዲቆም አዝዞ ሁለቱም ከሠረገላው ወርደው ሐዋርያ ፊልጶስ አጠመቀው ። የሐ-ሥራ ፰ ፣ ፳፮-፴ ይለናል ።

፰/ እንደዚህ ያለ ኃይለ ቃል በሐዋርያት ሥራ ስናነብ የሚያኮራን ነው ። ምክንያቱም ትንቢቱ የተነገረላቸው ሕዝቦች ቃሉን አንቀበለም ብለው መድኃኒታቸውን በመስቀል አስገድለው ፤ ደቀ መዛሙርቱንም በማሳደድ ላይ ሳሉ ኢትዮጵያ ብሉይ ኪዳንን ራሷ ተመራምራ ኢየሩሳሌም ድረስ መጥታ እንደተቀበለች ሐዲስ ኪዳንንም እንደዚሁ ያንድም ሐዋርያ ደም ሳታፈስ መጀመሪያው የኢትዮጵያ ሰው ወደ ቅድስት ሀገር ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረው ትንቢት መፈጸሙን በሐዋርያው ቃል ተረድቶ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ ፤ ብሎ በሐዋርያው እጅ ጥምቀት መቀበሉን በሐዋርያት ሥራ ሲነበብ መኖሩ ኢትዮጵያዊን ክርስቲያን ሁሉን ሲያኮራ የሚኖር ታላቅ ዕድል እንደሆነ መረዳት ያሻናል ።

፱/ የኢትዮጵያ ወጣቶች ሆይ ፡ ኢየሩሳሌም ለኢትዮጵያችን እንደዚህ ባለ ምስክርነት የተረጋገጠ የሃይማኖትና የመንግሥት መሠረት እንደሆነች ማወቅና መረዳትም ተገቢያችን ነው ፤ ስለሆነም ከዚህ ላይ አንድ ማስጠንቀቂያ መስጠት ተገቢ ይመስለኛል ፤ ንግሥተ ሳባ ፤ ከሰሎሞን ቀዳማዊ ምኒልክን እንደወለደች የሚነገረው በኢትዮጵያችን ታሪክ ውስጥ ነው እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ እንዳልተገለጸ ማወቅ ግድ ይገባል ፤ እሥራኤሎች ይህን ታሪክ ከዜና መዋዕል ያላገቡት ኩሩዎች ነበሩና ሰሎሞን ከአፍሪካዊት ሴት ወለደ እንዳ ይባል ያፈሩ ይመስለኛል ።



ሦስተኛ ስለ ኢትዮጵያ ማኅበር ገድልና ስለ ኢትዮጵያ ቅዱሳት መካናት መብት ።

፩/ በላይኛው መሥመር እንደተነገረው ኢትዮጵያ በሕንደኬ ንግሥት ዘመነ መንግሥት በዘመነ ሐዋርያት ፤ ከሐዋርያ ፊልጶስ እጅ የተቀበለችውን እምነትንና ጥምቀትን ጠብቃ ስትኖር ፤ አሁንም በነገሥታቱ አስተዋይነት ፤ አራተኛው መቶ ዓመት ሲጀመር የእምነተ ወንጌልን ሥርዓት የሚያስረዳ መምህር ለማስመጣት ፍሬምናጦስ የተባለውን ሰው አቅራቢያቸው ወደ ሆነው አገር ወደ ግብፅ ልከው አባ አትናቴዎስ የእስክንድርያ ፓትረያርክ ፍሬ ምናጦስን ተቀብለው ራሱን ሥርዓተ ክህነትን አስተምረው የጳጳስነትን ሥልጣን ሰጥተውት አባ ሰላማ ተብሎ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ ፡ በተሰጠው ሥልጣን ወንጌልን ባስተማረ ጊዜ ፤ በስብከተ ወንጌል የጌታችን ፍቅር ያደረባቸው ኢትዮጵያውያን ፡ ስለ ክርስቶስ ፍቅር ሥርዓተ ዓለምን ንቀው ፣ ሥርዓተ ምንኩስናን የተቀበሉ መናንያን መነኮሳት በሚያስደንቅ መንፈሳዊነት ተነሥተው የሱዳንና የምድረ ግብፅን በረሃ አቋርጠው ጌታችን ንጹሕ ደሙን ወደ አፈሰሰባት ወደ ኢየሩሳሌም ሔደው ለመንፈሳዊ ምግባርና ትሩፋት ጽሙዳን ሆነው ጌታችን በተወለደበት በቤተ ልሔም በተጠመቀበት በዮርዳኖስ በተሰቀለበት በቀራንዮ ፤ በተቀበረበት በጎልጎታ በዚሁ ሁሉ በቅዱሳት መካናት ቦታ ገዳም አቅንተው ሥርዓተ ማኅበር ሠርተው በመኖራቸው ለኢትዮጵያ አስደናቂ የሆነ የቅዱሳት መካናት ይዞታና የሃይማኖት አገልግሎት በቀደምትነት አውርሰውታል።

፪/ ይህም ይታወቅ ዘንድ በዚህ በሚያስደንቅ መንፈሳዊነታቸው የክርስቲያን ማኅበር ሁሉም ባንድነት የክርስቶስን ትንሣኤ በሚያከብሩበት በታላቁ በዓል ቀን ብርሃን ለማውጣት በተቀዳሚነት ወደ ጌታችን መቃብር መጀመሪያ የሚገባ የኢትዮጵያ ገዳም አለቃ እንደ ነበረ የሚያስረዳ የክርስቲያን ማኅበሮች ሁሉም የተስማሙበት ፤ የሀገሩ ገዥዎች ያጸደቁት መረጃ በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ ከነፎቶ ኮፒው የመጀመሪያውን ገጽ ይዞ ይገኛል ። ፳፩ ፣ ፳፫

፫/ ኢትዮጵያውያን ሆይ ፤ እነዚህ ገድለኞች የኢትዮጵያ መነኮሳት ፡ ኢትዮጵያ በቱርኮች በተከበበች ጊዜ መገናኛው መንገድ ተቋርጦባቸው ፡ ከኢትዮጵያ ረዳት አጥተው ከ፲፯ኛው መቶ ዘመን ጀምሮ ያገኛቸው የኑሮ ችግርና ጊዜ ከረዳቸው ከሌሎች የክርስቲያን ማኅበሮች ዘንድ የደረሰባቸውን መጉላላትና የንብረታቸውን መነጠቅ በጠቅላላውም የተቀበሉት ግፍና የተፈጸመባቸው የዓመጽ ተግባር እጅግ አሳዛኝ ነው ። እነሱ በረኃብና በዕርቃን ተይዘው ንብረታቸውና የቅድስና ይዞታቸውን ለመውረስ ሌሎች የክርስቲያን ወገን ድርጅቶች ሲጣሉበት በመመልከት ጽኑ ፈተና ተቀብለዋል ። ይህንንም የክርስቲያኖችን ዓመጽና በአፅመ ርስታችሁና በወገኖቻችሁም የደረሰውን ሁናቴ ትረዱት ዘንድ ይኸውና ማስረጃውን ሁሉ ሰብስቤ ፤ አቅርቤላችኋለሁ ።

www.ethiopianorthodox.org



(አፄ ዮሐንስ ፬ኛ)

፬/ አፄ ዮሐንስ ገና አባ በዝብዝ ካሣ ሲባሉ ጀምረው ገዳሙንና ማኅበሩንም ለመርዳት እጅግ ከፍ ያለ ጥረት ቢያደርጉም በዘመናቸው የነበረው የቱርኮች ጠበኛነት ፖለቲካ ባይረዳቸው ፤ ለማኅበሩ መተዳደሪያ ገንዘብና ሌላ የማረፊያ ቦታ ገዝተው ከመስጠት በቀር በቅዱሳት መካናት አ... ጉዳይ የደረሰባቸውን ጥቃት ለማስወገድ ጊዜ አልረዳቸውም ።

www.ethiopianorthodox.org



<u>የኢትዮጵያ ን. ነ. ዳግማዊ ምኒልክ ።</u>

፳/ ይኸውም የማኅበሩ ጩኸት በይበልጥ እስከ ዳግማዊ ምኒልክ ዘመን ተላልፎ ዳግማዊ ምኒልክና ባለቤታቸው እቴጌ ጣይቱም ይህን ጥቃት ለማስ ወገድ ከፍ ባለ ጥረት ተነሥተው በደጃዝማች መሸሻ ወርቄ መላክተኛነት ብዙ ሀብት ወጪ በማድረግና ሊነገር በማይቻል ዘዴም ብዙ የደከሙበት መሆኑ ቢታ ወቅም በዴር ሡልጣን ገዳም ለማኅበሩ በተለይ መናፈሻ መውጫ በር በማስ ከፈትና ለማኅበሩ መርጃ ገንዘብና የሚከራይ ቤት ከማሠራት በቀር በግብፆችና በአርመኖች አጥቂነት በንብረታቸውና በገዳማቸው ከደረሰው ጥቃት ነፃ ሊያ ወጧቸው ጊዜ አልረዳቸውም ።

www.ethiopianorthodox.org



ግርማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ በልዑል አልጋ ወራሽነት ።

www.ethiopianorthodox.org

## ትዕግሥትና ዕውቀት ።

## ከልጅነት እስከ ሺበት ።

# ግርማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ በልዑል አልጋ ወራሽነት ።

፩/ የሰው ፍጥረት ሁሉ ካለማወቅ ወደ ማወቅ በተሻሻለበት በአዲሱ መለ ዋወጫ ዘመን መካከል ኢትዮጵያ ተለይታ ወደኋላ መቅረቷን የተመለከተው ፈጣሪ አምላክ በመለኮታዊ ጥበቡ ኢትዮጵያን በሥጋዊው መንግሥትና በመን ፈሳዊውም ሃይማኖት የሰው ፍጥረት ሊደርስባቸው ከሚቻለው ከሥልጣኔ ደረጃ ለማድረስ ባደረገው ከሃሊነቱ ለኢትዮጵያ ዕድገት ለሚሠራው የኢትዮ ጵያ ልማት ሥራ ሠሪ ያደርጋቸው ዘንድ ገና ሲፈጠሩ ትዕግሥትንና የአርቆ አስተዋይነትን ዕውቀት አዋሕዶ የፈጠራቸውን ልጅ ተፈሪ መኰንንን ኢትዮ ጵያ በሥጋዊ ኃይልና ጉልበት ብቻ ድንበርዋን ካለማስደፈር ሥራ በቀር ሌላ ዘመናዊ መሻሻል ሳይኖራት በልማድ ሰንሰለት ታሥራ በዘመናዊ ትምህርትና ሥልጣኔ ከመሻሻል ተለይታ በጥንታዊ ባህልና ልማድ ማዕበል ጠልቃ ጠቢባ ንን እየነቀፈች ስትኖር ፤ ከሃሊ አምላክ ደቂቀ እሥራኤልን በምሕረት በተመለ ከተበት ጊዜ ሙሴን መሪ እንዳስነሣላቸው ሁሉ ኢትዮጵያንም ከነበረችበት የከንቱ ልማድ ጨለማ ለማላቀቅ ቅዱስ ፈቃዱ በሆነ ጊዜ ከብዙ ኃያላን መካ ከል በዕውቀት የረቀቀውን በመንፈሳዊ ኃይል የላቀውን ወጣት መርጦ ከኢት ዮጵያ ምሥራቅ ጫፍ ከሐረር ክፍለ አገር ደጃዝማች ተፈሪ መኰንንን ለኢትዮ ጵያ መንግሥት ሕዝብ የሥልጣኔ መሪነትን መረጠ ።

ይኸውም የእግዚአብሔር መራጭነት ይታወቅ ዘንድ የኢትዮጵያ መሳ ፍንትና መኳንንት ባንድ ቃል መክሮ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱን ከፋሌ አም ጥቶ ንግሥተ ነገሥታት ብሎ በአባታቸው ዙፋን ባስቀመጠ ጊዜ ፤ ደጃዝማች ተፈሪ መኰንንንም ከሐረር አምጥቶ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ልዑል ራስ ተፈሪ መኰንን ብሎ በሕዝብ ምርጫ ሾማቸው ።

፪/ የሥልጣኔ ጉዞ ፤ በዚህ ጊዜ በዕውቀት የረቀቁ ወጣቱ የኢትዮጵያ መንግሥት መሪ በ፲፱፻፱ ዓ. ም. መስከረም ፲፯ ቀን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ራስ ተፈሪ ተብለው እንደተሾሙ ባገሩ ላይ ሰፍሮ የቆየውን ከባድ የልማድን ኃይል በጉልበት ልጋፈጠው ሳይሉ (ሽምግ ልና) ከላይ በመነሻው ትዕግሥትና ዕውቀት ከልጅነት እስከ ሺበት እንዳል ነው ለጊዜው ልማድን እንደልማዱ ታግሠው በሰላማዊ ርምጃ ለማሸነፍ ባላ ቸው ጥበብ መሳፍንቱና መኳንንቱን በርእይ (በማየት) ለማሠልጠን አገራቸው ኢትዮጵያንም ከሠለጠነው ዓለም አስተዋውቀው ከዓለም መንግሥታት ማኅ በር አንድነት ለማግባትና በመንፈሳዊ በኩልም ወደ ቅድስት ሀገር ሔደው

www.ethiopianorthodox.org

በኢየሩሳሌም የሚገኙትን የኢትዮጵያን ቅዱሳት መካናትን ጐብኝተው ኢትዮጵያ ን የሥጋዊና የመንፈሳዊም ዕድሏን ባንድነት አያይዘው አንድ ላይ ለማሳደግ ባላቸው አርቆ ተመልካችነት ዕቅድ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት መሪነት በተቀበሉ በ፯ኛው ዓመት የኢትዮጵያን መሳፍንቱንና መኳንንቱን አስከትለው ጥበቡን ለመገብየት ከኢትዮጵያ ወደ ሠለጠነው ዓለም ወደ አውሮጳ ጉዞ ጀመሩ ። ከአዲስ አበባ በምድር ባቡር እስከ ጂቡቲ ከዚያም በባሕር መርከብ እስከ ስዌዝ ከዚያም እስከ ኢየሩሳሌም ። በምድር ባቡር ተጉዘው ደረሱና በሚያዝያ ፲፰ ቀን ፲፱፻፲፮ ዓ.ም. ኢየሩሳሌም ሲገቡ የእንግሊዝ መንግሥት ባለሥልጣኖችና የሃይማኖት ባለ ሥልጣኖችም ሁሉ በየክፍላቸው ከፍ ባለ አቀባበል ተቀበሏቸው ።

ልዑል አልጋ ወራሽ ጉዟቸውን አስቀድመው ወደ ኢየሩሳሌም ያመሩት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተነሡበትን ሐሳብ ለመፈጸም እንዲያቃናላቸው በቅዱስ መቃብሩ ጸሎት አቅርበው ወዲያውም በቅዱሳት መካናት ያላቸውን መንፈሳዊ ሁናቴ አስቀድመው ተመልክተው ወደፊት ሊያሠሩት የሚገባቸውን ጉዳይ በማጥናት እንዲጠቀሙበት አስበው እንደሆነ የሚከተለው ሥራቸው ያስረዳናል ።

## ከደስታና ክብር ።

### ፫/ የልዑል አልጋ ወራሽ መንፈሳዊ ቅንዓት በቅዱሳት መካናት ፤

ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ኢየሩሳሌም ከገቡ ጀምሮ በጌታችን መቃብር በጎልጎታ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየዞሩ ሥፍራውን ሁሉ ሲያዩ ይህ የግሪኮች ሥፍራ ነው ፤ ይህ የላቲኖች ሥፍራ ነው ፤ ይህ የአርመኖች ሥፍራ ነው ፤ ይህ የሶርያዎች ሥፍራ ነው ፤ ይህ የግብፆች ሥፍራ ነው ፤ እያሉ ሲነግሩዋቸው ይህ የኢትዮጵያውያን ሥፍራ ነው ብሎ የሚነግራቸው አላገኙም ። በቀድሞ ዘመን ኢትዮጵያዎች በጎልጎታ ውስጥ ምንም ቦታ ቢኖራቸውና ቢቀድስ ዛሬ የኢትዮጵያዎች ቦታ ይህ ነው ባለመባሉ ልዑል አልጋ ወራሽ እጅግ አዘኑ ።

በጎልጎታም ውስጥ ብዙ ቦታ የያዙ ግሪኮች መሆናቸውን አውቀው ነበርና በአዲስ አበባ የሚኖረው ዶክተር ዘርቦስ ለጊዜው በኢየሩሳሌም ስለነበረ አስጠርተው የግሪክ ፓትሪያርክ አባ ድምያኖስ ለኢትዮጵያ መነኮሳት መቀደሻ የሚሆን በጎልጎታ ውስጥ አንድ ሥፍራ ቢሰጡኝ ብዬ አስቢአለሁና ይህንን አሳቤን አስታውቃቸው አሉት ፤ ዶክተር ዜርቦስም ሔዶ ይህንኑ አሳብ ነገራቸው አባ ድምያኖስም ነገሩን ለማኅበሩ አስታውቀው የልዑል አልጋ ወራሽን አሳብ በደስታ ተቀበሉ ።

ነገሩም በተቆረጠ ጊዜ አባ ድምያኖስ ከማኅበሩ ዋና ዋናውን ጨምረው ወደ ጎልጎታ ሔደው ለልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የሚሰጡትን ቦታ አይተው ተመለሱ ።



በማግሥቱም ከልዑል አልጋ ወራሽ ጋራ ባንድነት ሥፍራውን ለማየት ወደ ጎልጎታ ሔዱ ። ፓትሪያርክ አባ ድምያኖስ ለኢትዮጵያ ገዳም ለዴር ሥልጣን አቅራቢያ የሆነውን የአብርሃም ገዳም የሚባለውን ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ኢየሩሳሌም ለመድረሳቸው መታሰቢያ እንዲሆን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሰጥተናል ብለው በማኅበሩ መካከል ተናገሩ ። ልዑል አልጋ ወራሽም ይህ ነገር በመፈጸሙ እጅግ አድርጎ ደስ አላቸው ። ደስታቸውም ስለሁለት ነገር ነው ።

መጀመሪያ የኢትዮጵያ መነኮሳት በጎልጎታ ውስጥ የመቀደሻ ሥፍራ የላቸውምና የመቀደሻ ሥፍራ በመገኘቱ ደስ አላቸው ።

ሁለተኛም ቦታው ለኢትዮጵያ ለዴር ሥልጣን አቅራቢያ በመሆኑና የተያያዘ በመሆኑ ደስ አላቸው ።

ይኸውም የአብርሃም ገዳም የሚባለው ቦታ በቀድሞ ዘመን የተሠራ ስለሆነ አሁን በኖራና በቀለም ከማደስ በቀር ሌላ ኪሣራ የለበትም ።

ከዚህም በኋላ ውሉን ተጻጽፈው በፓትሪያርክ በአባ ድምያኖስ ፊርማና በማኅበሩ ማኅተም ታትሞ ለልዑል አልጋ ወራሽ ተሰጠ ።

ልዑል አልጋ ወራሽም ነገሩ በጣም እንዲጠነክርና ለማፍረስ ምክንያት እንዳይገኝበት ብለው ለዚህ ለአብርሃም ገዳም ለውጥ የሚሆን ከኢትዮጵያ ውስጥ ስድስት ጋሻ መሬት ለፓትሪያርክ እንሰጣለን አሉና ተዋደው ተፈራረሙ ።

ስድስት ጋሻ መሬት ለዚህ በጎልጎታ ውስጥ ላለው ለአብርሃም ገዳም ዋጋ ሆኖ አይደለም ። በዋጋ ቢሆን እስከ ሦስት መቶ ሺ ብር እናገኝበታለን ይላሉ ። ነገር ግን ፓትሪያርክ አባ ድምያኖስ ልዑል አልጋ ወራሽ ኢየሩሳሌም ለመድረሳቸው መታሰቢያ ይሁን ብለው ይህን እጅግ የከበረ ቦታ ስለሰጡ ይህም ስድስት ጋሻ መሬት ለአባ ድምያኖስ እንደመታሰቢያ እንዲሆን ብለን እንሰጣለን አሏቸው ።

በኢየሩሳሌም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ስለተሰጠው ስለአብርሃም ገዳም በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ በልዑል ተፈሪ መኰንንና በኢየሩሳሌም ፓትሪያርክ በብፁዕ ምገር ድምያኖስ መካከል የተደረገ የመስማማት ውል ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ልዑል ተፈሪ መኰንንና የኢየሩሳሌም ፓትሪያርክ ብፁዕ ምገር ድምያኖስ ከዚህ በሚከተለው ተስማምተዋል ።

#### መ ጀ መ ሪ ያ ።

ብፁዕ ፓትሪያርክ የኢየሩሳሌምና የፓለስቲና ሁሉ ፓትሪያርክ እንደመሆናቸው መጠን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ተፈሪ መኰንን ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌምን ለመሳለም በመምጣታቸው ምክንያት ለኢት

www.ethiopianorthodox.org

ቴዎስ ስለታመሙ ከኢየሩሳሌም ወደ ምድረ ግብፅ ወርደው ነበርና የዶር ሥልጣንን ነገር ለመነጋገርና ለመጨረስ ሳይመች ቀረ ።

ልዑል አልጋ ወራሽም ከኢየሩሳሌም ወደ ምድረ ግብፅ መውረዳቸው እርግጥ ሆኖ ነበርና እዚያ በወረድሁ ጊዜ ነገሩን እጀምራለሁ ብለው ነገሩ ሁሉ በፍቅር እንዲያልቅ የሚያመለክት ደብዳቤ ጽፈው ወደ አቡነ ጢሞቴዎስ ላኩ ።

## ለግብፃዊው ጳጳስ የተጻፈ ደብዳቤ ።

ወደ አቡነ ጢሞቴዎስ መላካቸው ምንም ዋናው ፓትሪያርክ አቡነ ቄርሎስ ቢሆኑ በኢየሩሳሌም የግብፆች ጳጳስ አቡነ ጢሞቴዎስ ስለሆኑ ነገሩን በጣም ያውቁታልና እርሳቸው በነገሩ እንዲያስቡበትና ከኢትዮጵያዎችና ከግብፆች መካከል ጠብ እንዲጠፋ ፍቅር እንዲሰፋ ይሆናል ብለው ነው ፤ ወደ አቡነ ጢሞቴዎስም የተላከው ቃል ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው ።

ይድረስ ከክቡር አቡነ ጢሞቴዎስ የኮፕት ኦርቶዶክስ ሊቀ ጳጳስ ፤ በኢየሩሳሌም ለሊቀ ጳጳሳነትዎ የሚገባ ሰላምታ አቀርባለሁ ።

በኢየሩሳሌም የምንገናኝ መስሎኝ የወዳጅነት ሐሳቤን ሁሉ በቃል እነጋገራለሁ ብዬ ደስ ብሎኝ ነበር ፤ ነገር ግን በካይሮ መሆንዎንና መታመምዎን ስዊስ ላይ በቴሌግራም ቢያስታውቁኝ እጅግ አዘንሁ ደግሞ ኢየሩሳሌም በደኅና ስለ መግባት በጻፉልኝ ደብዳቤ እጅግ ደስ ብሎኛል ።

አሁንም በቃል አነጋግርዎታለሁ ብዬ ያሰብሁትን የወዳጅነት አሳቤን ከዚህ ቀጥሎ ጽፌ ልኬልዎታለሁና አስበውበት እንዲቆዩና ካይሮ በመጣሁ ጊዜ ተነጋግረን ሐሳቤን እንዲፈጽሙልኝ ተስፋ አደርጋለሁ ። ዓለም ሁሉ በሕግና በአምልኮት ፈጽሞ ተራርቆ ሲኖር ግብፅና ኢትዮጵያ ከሁሉ አስቀድሞ እንደ ተቃረቡና እንደ ተገናኙ የዓለም ታሪክ ሁሉ ይመሰክራል ።

ደግሞ ከዚያ በኋላ የተቃረቡና የተገናኙ ዓለሞች እንደገና እየተለያዩ ሲኖሩ ግብፅና ኢትዮጵያ ምንም የተለያዩበት ጊዜ የለም ።

ነገር ግን አሁን በቅርቡ ዘመን በተጀመረው በኢየሩሳሌም ቦታ ነገር በመካከላችን ትንሽ ነገር በመነሣቱ መንግሥታችንም ሕዝቡም በጣም አዝነዋል ቀድሞም በአፄ ምኒልክ በሁለቱ አባትና ልጅ መካከል የተነሣው ይህ ነገር አለክርክር በወዳጅነት እንዲፈጸም አስበው ሳሉ ነገሩ ሳይፈጸም በተሎ ዓረፉ ከዚያም ወዲህ እኛ ይህ ነገር በወዳጅነት እንዲፈጸም ብለን ወደ ፓትሪያርክ አቡነ ቄርሎስና ወደ ንጉሥ ፉዓድ መልእክተኞች ልከን ነበር ። ነገር ግን ጊዜው ባይደርስ እስካሁን ሳይፈጸም ቆየ ።

አሁንም ይህ ነገር አለክርክር በወዳጅነት እንዲጨረስ ብለን አስበን መጥተናልና የርስዎም ሐሳብ እንደዚሁ ቢሆን መልካም ነው በዳኛ ፊት ተቋቁመን



እኛም ብንወስደው እናንተም ብትወስዱት ጠብ እየበዛና እየተራራቅን ከመሔድ በቀር ሌላ ትርፍ የለበትም ደግሞ ግብፆችና የኢትዮጵያ ሰዎች አባትና ልጅ ሆነው ሲኖሩ በቦታ ነገር ተጣልተዋል ቤተ ክርስቲያኑም ቅዳሴ እንዳይቀደስበት ተዘጋ ተብሎ ስለ ተወራ ከእኛ በሃይማኖት የተለያዩ ሰዎች ሁሉ ታላቅ ደስታ እንዳደረጉ የታወቀ ነው ፤ ደግሞስ በማያልፈው በሃይማኖት ነገር አንድ ሆነን ስንኖር በሚያልፈው በቦታ ነገር ብንለያይ ጥቅማችን ምንድር ነው ? ስለዚህ እርስዎ ይህን አቅልለው እንዲጨርሱ ለማድረግ እንዲችሉ አንጠራጠርም ።

አሁንም በእናንተ በአባቶቻችንና በእኛ መካከል ሰይጣን ያኖረውን የእንቅፋት ደንጊያ እርስዎ አንሥተው ቢጥሉት በግብፅና በኢትዮጵያ መካከል ዘለዓለም የኖረውን ወዳጅነት እንዳይናወጥ ማድረገዎን ያስረዳል ። በታሪካችን ውስጥ ስምዎ አለመረሳቱን እናሳስብዎታለን ። ይልቁንም እኔ ወደ ኢየሩሳሌም እንግዳ ሁኜ የመጣሁበት ዋናው ነገር የዚሁኑ የገዳማችንን ነገር በፍቅርና በወዳጅነት ለመጨረስ ነውና እንግድነቴን አክብረው ይህን ነገር ቢጨርሱልኝ የማይረሳ ወሮታ ነው ለእኔም ትልቅ ክብር ስለሆነ ፤ በኔና በእርስዎ መካከል የተለየ ወዳጅነትና የመተሳሰብ መሠረት በመቆሙ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ደስ እንዲለው ጥርጥር የለበትም ። ሚያዝያ ፲፰ ቀን ፲፱፻፲፮ ዓ. ም. በየኢሩሳሌም ተጻፈ (በደስታና ክብር ገጽ ፲፫-፲፭)

ልዑልነታቸው ኢየሩሳሌም ሆነው ለኢየሩሳሌም ጳጳስ ከዚህ በላይ የተገለጠውን ደብዳቤ ጻፉ ።

፮ኛ/ በኋላም ከኢየሩሰሌም ወደ ካይሮ እንደተመለሱ ሚያዝያ ፳፮ ቀን ከብፁዕ ፓትሪያርክ አቡነ ቄርሎስ ለመገናኘትና በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ለማስቀደስ ከመሔዳቸው በፊት አስቀድመው ማታውን ከዚህ የሚከተለውን ሽልማት ላኩላቸው ።

## ሽልማት ።

አንድ በወርቅና በፈርጥ ያጌጠ የሊቀ ጳጳስ አክሊል
ሁለተኛ አንድ ካባ ላንቃ ከነ መደረቢያው
» አንድ የአረንጓዴ ሐር ሕባኔ
» በወርቅ የተጠለፈ የአረንጓዴ ከፋይ ሱሪ
» ድርብና አንድ አብደላካኒ እጀ ሰፊ ቀሚስ
» የወርቅ ጥልፍ ሰቅ (መታጠቂያ)
አንድ ገበታው በወርቅ ያጌጠ አርባዕቱ ወንጌል የብራና
» የወርቅ መቋሚያ
» የወርቅ የእጅ መስቀል ።

www.ethiopianorthodox.org

ይህን ከዚህ በላይ የተዘረዘረውን ሽልማት ሸለምዋቸው ። (ደስታና ክብር ገጽ ፷፬) ይኸውም ስጦታ በደረሱበት ሁሉ ለገዳማትና ለአብያተ ክርስቲያናት ለትምህርት ቤቶችም ከሚሰጡት የገንዘብ ስጦታ ሌላ ነው ፤ ይህን ሁሉ መንፈሳዊ ፍቅር የመላው ጉብኝት ፈጽመው ወደ አውሮጳ ጉዞ ቀጠሉ ።

፫ኛ/ <u>የኢትዮጵያ መንግሥት</u> አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ፡ የኢትዮጵያን መንግሥት ከዓለም መንግሥታት ማኅበር አንድነት አባል በማድረግና ከሙሉ ኤሮጳ መንግሥታትም ጋር በማስተዋወቅ አስደናቂ የሆነ ተግባራቸውን ፈጽመው ሲመለሱ የኮፕቶች ቤተ ክርስቲያን ማኅበሮችም እንደዚሁ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያንና የግብፅን አንድነት በኅብረት የሚያስደስት የፍቅርና የወንድማማችነት መልስ ያቈዩኛል በማለት የነበራቸውን ተስፋ ለውጠው አሳዛኝ የሆነ ቃል ስለአቆዩዋቸው ከልዑልነታቸው የተነገረው ቃል ።

«የኢየሩሳሌም ገዳማችን ነገር የግብፅ ማኅበር የመለሱት መልስ ደስ የማያሰኝ ሆነብን ሲሉ ልዑል አልጋ ወራሽ በዚህ ነገር እጅግ አዘኑ ፤ እንኳን እኔ ራሴ መጥቼና መላክተኛ ብንልክ በማክበር ተቀብለው ደስ አሰኝተው የሚመልሱት ይመስለኝ ነበር እንጂ ፤ በአባቶችና በልጆች መካከል ይህን የመሰለ ነገር የሚሆን አይመስለኝም ነበር እያሉ ለመኳንንቶቻቸው ነገሩዋቸው ።

የግብፅም ማኅበር ልዑል አልጋ ወራሽ በነገሩ ማዘናቸውን በሰሙ ጊዜ የላኩልንን ደብዳቤ የተረጐመልን ሰው በነገሩ ተሳስቶ የማይገባ ቃል ጽፈውላችኋል ብሎ ስለ ነገረን በዚህ አዝነን ነው ብለው ምሥጢራቸውን አውጥተው ተናገሩ ልዑል አልጋ ወራሽ በዚህ ነገር ከፊተኛው የበለጠ አዘኑ ፤ የላኩባቸውንም ደብዳቤ አሳዩኝ ቢሏቸው ለጊዜው አናገኘውም አሉ ።

ለዚሁም ጉዳይ ወደ ሆቴል መጥተው የነበሩት የግብፅ አማካሪዎች ስማቸው ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው ፤ ፋዚ ኤል ሞኒ ፣ ፓሻ ማርቆስ ሱሚካ ፤ ፓሻ ቶማስ ቡርስ ፤ ዓብደል ማሌክ የአኪም ሚካኤል ቤይ ናቸው ። በኋላ ግን ጋላጊ ፓሻ የሚባለውም አለ ፤ እኔ ነገሩን እንዲቀና አደርጋለሁ አንድ የታመነ ሰው ትተው ይሂዱ ብለው ለልዑል አልጋ ወራሽ አመለከቱ፡ እርሳቸውም ዋና የምሥጢር ጸሐፊያቸውን አቶ ተክለ ማርቆስን አጋጠሙ ። ( ደስታና ክብር ገጽ ፩፻፶ ) ነገር ከሥሩ ውኃ ከጥሩ እንዲባል ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በወጣትነት የወሰኑትን የትዕግሥትን አመራር ከዚህ በላይ ለአንባቢዎች ከገለጽሁ ዘንድ ታሪኩን እስከ ፍጻሜ እንደሚከተለው እቀጥላለሁ ።

## ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አፄ ኃይለ ሥላሴ ።

፩/ ከላይ በተቀዳሚው ገጽ «ትዕግሥትና ዕውቀት» ከልጅነት እስከ ሺበት» በሚል መነሻ እንደተገለጸው ጊዜ ረድቶት በሰው ላይ ሠልጥኖ የቆየውን ያለማወቅና የግብዝነትን ኃይል በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ በገጠማቸው ሥፍራ ሁሉ ፈጣሪ አምላክ በለገሣቸው ትዕግሥት አለፉት እንጂ ባለኝ ሥል





ግርማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ የንጉሠ ነገሥትነት ዘውድ እንደተቀዳጁ ።

www.ethiopianorthodox.org

ጣን ልጠቀምበት ያሉበት ጊዜ አልነበረም ሁሉንም በትዕግሥት ችለው፤ «ኢትማእ በእኩይ፤ አላ ማዖ ለእኩይ በገቢረ ሠናይ፤ እንዳለው (ሮሜ ፲፪ ፡ ፳፩) «ክፉውን በመልካም ግብር ላሸንፍ እንጂ በክፉ ላሸንፍ ሳይሉ» በኃይል ፈንታ ከክረምት ጨለማ የከፋውን ያለማወቅን ጠባይ ፤ በትምህርት ለማራቅ ብቻ ገጠሙት፤ ለሕዝብ በሚገባው ቋንቋ ቅዱሳት መጻሕፍትን በማሳተም ጀምረው ብርሃንና ሰላም የተባለውን ፈጥኖ ደራሽ አብሳሪ ጋዜጣ እያሳተሙ በየደጁ ደርሶ ዓይነ ልቡናን የሚያበራ፤ የሰላም መብራት በመላክ ድንቁርናን ዓይነ ጥላውን ገፈው ጣሉለትና ኢትዮጵያዊ ሁሉ ክፉና ደጉን ወደ ማወቅ ባዘነበለ ጊዜ በዕውቀት ፋና ይመሩት ጀመር ።

ሀ. «አባቶቻችን ግብፃውያን የኢትዮጵያ ሰዎች ከሊቃውንቶቻቸው ወገን በራሳቸው ፈቃድ ሊቀ ጳጳሳትን ለራሳቸው አይሹሙ ብለውናል ይሉት የነበረውን ከንቱ ልማድ ጠንቃቃው መሪ ተፈሪ መኰንን ለግራ ቀኙም በማይቆረቁር ፍልስፍናዊ ጥበብ በ፲፱፻፳፩ ዓ. ም. ከአንድ ግብፃዊ ሊቀ ጳጳስ ጋራ አምስት ከኢትዮጵያ መምህራን ጳጳሳት በማሾም ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያዊን ሰውነት የጳጳስነትን መዓርግ ለመልበስ አበቁት፤ በዚህ ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በበጎች ባለቤትና በቅጥረኛው እረኛ መስሎ ያስተማረው ቃል ምሥጢር በኢትዮጵያ ምድር ተተረጐመ፤ ዮሐንስ፤ ም. ፲ ፡ ፲፪. ፲፫

እንደዚህም ማለት በኢትዮጵያ ላይ ባለቤትና ምንደኛ የሚፈተንበት ኃይል ድንገት ከሰማይ በወረደ ጊዜ ተወላጆቹ እረኞች ከሞተው ሕዝባቸው ጋራ አብረው ሞቱ፤ ከተሰደደው ጋራ አብረው ተሰደዱ፤ ከታሠረው ጋራ አብረው ታሠሩ ። ቅጥረኛውሳ ?

እግዚአብሔር በዚህ ጊዜ ከዚያ በፊት በኢትዮጵያ ምድር ላይ ደርሶ የማይታወቀውን እንደዚህ ያለውን የሰው እልቂት ፈተና ያዘዘበት ስለምን ይሆን ? ብለን ምሥጢሩን ብንመረምር፤

፩ኛ/ ጌታችን ኢየሱስ በቃሉ ያስተማረውን ትምህርት ለኢትዮጵያ ሰው በከዊን ለማስረዳት፤ ይሆን ?

፪ኛ/ በግርማዊነታቸው ያሳደረውን የጸጋ ዕውቀት ትርጕሙን ለመግለጽ ይሆን ?

፫ኛ/ የሥጋ ትውልድን ሞያ ኢትዮጵያን ሁሉ ኢትዮጵያዊው ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ በመናገሻዩቱ ከተማ በአራዳ አደባባይ ለመሠዋት ቆመው ኢትዮጵያ እንኳንስ ሰው ምድሪቱም ለባዕድ እንዳትገዛ ገዝቻለሁ ባሉት ኃይለ ቃል ለኢትዮጵያ ትውልድ የሥጋ ልደትን ክብር ለማስተማር ያመጣው ይሆን ? ተብዬ ብጠየቅ እውነት የእግዚአብሔር ገንዘብ ናትና በከሃሊነቱ ለምስክርነት ካበቃኝ ስለ ፫ኛው ጥያቄ ትምህርት ይመስለኛል መርማሪው አባ ፊልጶስ ።

www.ethiopianorthodox.org

## አፄ ኃይለ ሥላሴ በማዕከላዊ ዘመን ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ጃንሆይ የወጣትነት ጊዜያቸውን ይህን በመሰለ ተአምራዊ ሥራ አሳልፈው መከራው አልፎ ያዲሱ ዘመን ደስታ እንደተተካም በማዕከላዊ ዘመናቸውም የዕውቀቱ መሪነታቸውን በመቀጠል ከላይ ከወረደው ፍልስፍናዊ ጥበብ አሁንም በቅጥረኛው ሊቀ ጳጳስ ሥፍራ ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳሳትን በውስጡም ጳጳሳትን እንዲሾሙ ተስማምተው በማሾማቸው በኢትዮጵያዊው ሊቀ ጳጳሳት ከተሾሙት ጳጳሳት አንዱ በሀገር ቅድስት በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ጳጳስ ተብሎ እንዲላክ ያደረጉበትንም ጥልቅ ምሥጢር ስመረምረው ከፍ ብሎ በተነገረው ጽሑፍ «እንኳንስ እኔ ራሴ መጥቼና መላክተኛም ብንልክ በማክበር ተቀብለው ደስ አሰኝተው የሚመልሱት ይመስለኝ ነበር እንጂ በአባቶችና በልጆች መካከል ይህን የመሰለ ነገር የሚሆን አይመስለኝም ነበር እያሉ ለመኳንንቶቻቸው ነገርዋቸው ሲል ደስታና ክብር የነገረንን የትዕግሥትዎን ትዝታ ያሳድርብኛል ።»

### ግርማዊ ጃንሆይ ፤

በዚህ ጊዜ ቀደምትዎ ነገሥታት ይህን የቅዱሳት መካናትን ጥቃት ለማስለቀቅ ብዙ የገንዘብና የሰው ጉልበት ሠዉተውበት ያልተቻለ ሲሆን ግርማዊነትዎ ለሰው ንብረቱ የሚጠበቀው በሰብአዊ መብቱ መሆኑን በማስተዋልዎ መብቱን በመብት አስወግደው በኢትዮጵያ ካኖሩት የቤተ ክርስቲያን የነፃነት መሠረት ሕንፃ ዘርፍ የመላው ዓለም መዲና በሆነችው በቅድስት ሀገር በኢየሩሳሌም በሥራ ተገኝቶ በግብፅ ጳጳስ ጭቆና ሥር የነበረው ኢትዮጵያዊ ማኅበርዎን ነፃ ለማውጣት በሀገር ቅድስት በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ጳጳስ ተብሎ እንዲላክ ባደረጉት ምሥጢር የኢትዮጵያ ገዳማት በራሱ ጳጳስ እንዲተዳደር በማድረግዎ በዴር ሥልጣን ያሉት የሐበሻ መነኮሳት የኛ እንግዶች ናቸው እንጂ ርስት የላቸውም አስተዳዳሪዎቻቸውም እኛ ነን እያሉ ግብፆች ይመኩበት የነበረውን ከንቱ ልማድ በሕጋዊ መሥመር ከዜጐችዎ ራስ ላይ እንዲነሣ ያደረጉበት ጥበብ ከጥበባት በላይ ነው ። የሕዝብዎ ውለታ መላሽ ያሰኝዎታል ።

በግርማዊነትዎ መሪነት የተላከው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ በዓለም ሕግ ፊት የክብር መብት ሥልጣን ለብሶ ከሥራ ሥልጣን ጓደኛው ከግብፃዊው ጳጳስ ጋራ ተካክሎ በዕሪና (በእኩልነት) ጐን ለጐን በመቆም ተከራክሮ ያለ ሕግ የተያዘውን የኢትዮጵያን ርስት በትክክለኛ ፍርድ ለማስመለስ ያስቻለው የግርማዊነትዎ ጥልቅ ዓላማ ምሥጢር ከአድናቆት በላይ መሆኑን ስገልጽ እኔም ለዚህ ለተቀደሰው መልእክት አንደኛ የኢትዮጵያ ጳጳስ ሆኜ በመገኘቴ ታላቅ ደስታና ክብር ይሰማኛል ።





በታላቅ ኃይል ፈተናውን ያለፈ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሰውነት በመዋዕለ ሲበት ።

www.ethiopianorthodox.org

፫/ የምርጫ ጉባኤ አባሎች ብዛት በድምሩ ፩፻፷፭ ሆኖ ከያንዳንዱ ክፍል የሚወጡት የምርጫ ጉባኤ አባሎች ቁጥር ፤

ሀ/ ከቅዱስ ሲኖዶስ አባሎች ፤
ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ፲፭
ለ/ ከዘውድ ምክር ቤት አማካሪዎች ፱
ሐ/ ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ፲፮
መ/ ከሕግ መወሰኛ ምክር ቤት በምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት የሚመረጡ ፰
ሠ/ ከሕግ መምሪያ ምክር ቤት በምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት የሚመረጡ ፲፭
ረ/ ከቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ጉባኤ የጉባኤው አባሎች ፱
ሰ/ ከየሀገረ ስብከቱ በቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ በሚከተለው ብዛት የሚጠሩ የገዳማት አበምኔቶችና ታላላቅ የደብር አለቆች ።

፩. ከአዲስ አበባ ------------------------- ፲፭
፪. ከሸዋ ጠቅላይ ግዛት ፰
፫. ከወሎ » » ፰
፬. ከትግሬ » » ፰
፭. ከኤርትራ » » ፰
፮. ከበጌምድርና ስሜን ጠቅላይ ግዛት ፰
፯. ከጐጃም ጠቅላይ ግዛት ፰
፰. ከሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት ፮
፱. ከአሩሲ » » ፬
፲. ከወለጋ » » ፬
፲፩. ከሲዳሞ » » ፬
፲፪. ከከፋ » » ፬
፲፫. ከኢሉባቦር » » ፫
፲፬. ከገሙ ጐፋ » » ፫
፲፭. ከባሌ » » ፪ ይሆናል ።

፬ኛ/ ምርጫውን ለማስፈጸም ከጳጳሳትና ከምእመናንም የተውጣጡ ሰባት (፯) አባሎች የሚገኙበት አንድ የአስመራጭ ኮሚቴ በቅዱስ ሲኖዶስ ይሾማል ። ከኮሚቴውም አንዱ የኮሚቴው ሰብሳቢ ፤ አንዱ ጸሐፊ ይሆናሉ ።

፭ኛ/ የኮሚቴው ተግባር ፤

ሀ/ መራጮች የምርጫ ድምፅ የሚሰጡበትን ወረቀት (ካርድ) በመራጮች ልክ ማዘጋጀት ፤



ለ/ ከዚህ በላይ በቍጥር ፫ እንደተመለከተው ከየክፍሉ የሚውጣጡት የመራጭ ጉባኤ አባሎች ከየክፍሉ የተወከሉበትን (የተመረጡበትን) ጽሑፍ በመቀበል ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ፤

ሐ/ የዕጩዎችን ስም ዝርዝር በሰሌዳ ጽፎ በምርጫው ቀን ለመራጮች ማስታወቅ ፤

መ/ ምርጫው በሚፈጸምበት ቀን ፤ የምርጫ ድምፅ መስጫው ወረቀት (ካርድ) ስም ያልተጻፈበት መሆኑን መርምሮ ለምርጫው ክፍል በአንድ ጠረጴዛ ላይ እንዲቀመጥ ማድረግ ፤

ሠ/ እያንዳንዱ መራጭ በተራ ወደ ድምፅ መስጫው ክፍል እየገባ አንዳንድ የምርጫ ድምፅ መስጫ ወረቀት (ካርድ) እያነሣ ከዕጩዎቹ መካከል የመረጠውን ሊቀ ጳጳሳት ስም ጽፎ ለዚሁ በተዘጋጀው አንድ ሳጥን ውስጥ ሲጨመር መመልከት ፤

ረ/ መራጮች የምርጫ ድምፅ ሰጥተው ሲያበቁ ሳጥኑን ከፍቶ ለያንዳንዱ ዕጩ የተሰጠውን ድምፅ ብዛት በጥንቃቄ ከቆጠረ በኋላ በቃለ ጉባኤው ተፈራርሞ በድምፅ ብልጫ የተመረጡትን ሊቀ ጳጳሳት ስም በቅዱስ ሲኖዶስ አማካይነት ለንጉሠ ነገሥቱ ማቅረብ ይሆናል ።

፮ኛ/ ለአሁኑ ምርጫው የሚፈጸምበት ዕለት መጋቢት ፳፰ ቀን ፲፱፻፷፫ ዓ. ም. እንዲሆን ሲወሰን ለወደፊቱ በፓትረያርኩ መሞት ምክንያት የፓትረያርኩ መንበር ባዶ በሆነበት በአርባ ቀን ውስጥ የምርጫው ሥነ ሥርዓት ይፈጸማል ።

፯ኛ/ ምርጫው ከሚደረግበት ዕለት ከስምንት ቀኖች አስቀድሞ ቅዱስ ሲኖዶስ ዝግ ስብሰባ አድርጎ ከኢትዮጵያ ሊቃነ ጳጳሳት መካከል በዕውቀት በትዕግሥትና በግብረ ገብነት ለፓትረያርክነት እውነት ይበቃሉ የሚላቸውን ከሦስት ያልበለጡ ዕጩዎች መርጦ ስማቸውን ለምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያስታውቃል ።

፰ኛ/ እንደዚሁም ቅዱስ ሲኖዶስ የነዚሁ የዕጩዎቹ ስም ዝርዝር በመንበረ ፓትሪያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን መንበር ላይ ተቀምጦ ለሦስት ቀን ጸሎተ ቅዳሴ እንዲደረስበት ያደርጋል ።

፱ኛ/ ምርጫው የሚፈጸመው በአዲስ አበባ ከተማ በመንበረ ፓትሪያርክ አዳራሽ ውስጥ ይሆናል ።

፲ኛ/ ምርጫው በምርጫ አስፈጻሚው ኮሚቴ አባሎች ፊት በምሥጢር ድምፅ አሰጣጥ ሥርዓት ይፈጸማል ።

፲፩ኛ/ የመራጭነት መብት ተሰጥቷቸው ከተጠሩ ሰዎች መካከል ከሦስት ሁለት እጁ በምርጫው ቀንና ሥፍራ ከተገኙ ምርጫው ሊደረግ ይችላል ።



www.ethiopianorthodox.org



ባስደናቂ ኃይል ለኢትዮጵያ ቤተ መቅደስ የተገኘነውን ሐዋርያዊውን አክ ሊል አስገኚው ንጉሠ ነገሥት በተገኙበት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥር ዓት ፤ ጸሎትና ቅዳሴ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የፓትሪያርክነታችን የክብር አክሊል እንደተቀዳጁ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ልዩ ማሳሰቢያ ።

## የመንፈሳዊ ዓላማ ፍጻሜ ።

## የቤተ ክርስቲያን አንድነት አሳብ ።

### ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሃይማኖት ጠባቂ ጃንሆይ ።

በአብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ የሃይማኖት ጠባቂ የሚል የክብር ስያሜ የተሰጠዎ እግዚአብሔር በሰው አድሮ ያናገረው ትንቢታዊ ቃል ነው እንጂ በከንቱ አይደለም ። እኔም ከጥንት ጀምሮ የምመኝልዎ በዚህ ከእግዚአብሔር ፈቃድ በተሰጠዎ መልካም ዕድል እስካሁን የፈጸሙት ሥራ ትንሽ ባይሆንም እስካሁን ከሠሩት ሥራ የበለጠ ቅዱስ ተግባር አሁንም ይጠብቅዎታል ። ይኸውም በማካሔዱ ላይ የሚገኙት የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን አንድነት ጉዳይ ነው ።

ስለዚሁም አስተያየት የሰዎችን ስመ ተጸዎአ ያንዳንዱን ድርጅት መጠሪያ ሳይመለከቱ አንድ ክርስቶስንና አሐቲ ቤተ ክርስቲያንን መሠረት በማድረግ ቤተ ክርስቲያንና የክርስቶስ ቤተሰብ ክርስቲያንንም ሁሉ ባንድ በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ለማዋሐድ ፈቃደ እግዚአብሔር በግልጽ ይረዳዎታል ይህ ሰማያዊ ዕድል እንዳያመልጥዎ በትሕትና አሳስባለሁ ።

## ማስታወሻ ።

ይህን የዓለም ሰው ሁሉ ልዩ ልዩ ባህልና የሃይማኖት ክፍል በሰፈነበት ከተማ በኢየሩሳሌም የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መሠረት በሆነች በጎልጎታ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚታየውም የፍጥረት መዘባበቻ የሆነው የክርስቲያን አስተዳደር ሁናቴ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከነፎቶ ኮፒው ተጽፎ እንደሚነበበው በ፲፰፻፵፯ ዓ. ም. ከጎልጎታ ባለሥልጣኖች ለቱርክ መንግሥት ቀርቦ በሕግ የጸደቀውን መረጃ በገጽ ፳፭ና ፳፫ ተመልከት ይህን የመሰለ አስተዳደር በማድረግ የቤተ ክርስቲያን አንድነት ጠቅላላ አስተዳደር መንፈሳዊ ጉባኤ መመሥረት በሚቻልበት አኳኋን ቀደምትነት ካላቸው አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ጋራ አስቀድመው ቢመካከሩበት ፈቃደ እግዚአብሔር እንደሚረዳዎ አምናለሁ ። ቃለ እግዚአብሔር ነው ።

ስለዚህ ኢትዮጵያ ባሁኑ ጊዜ ላገር ነፃነት ለሕዝብ እድገት የታደሉ አስተዋይ መሪ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ላነገሡላት ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብና ግርማዊነታቸውንም በጸሎት ማሰብ ይገባታል ።

## ማብራሪያ ለኢትዮጵያውያን ።

በዚሁም መጽሐፍ ውስጥ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የነበረውን ርስት መብት ለመረዳት ጠቃሚ የሆኑ ማስረጃዎች ይገኙበታል ። እነዚህም የሚከተሉት ናቸው ።



www.ethiopianorthodox.org

፭ኛ/ በጎልጎታ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ የሚገኙት የክርስቲያን ማኅበሮች መሪ ዎች ሁሉ የቅዳሜ ሥዑር ዕለት የትንሣኤን በዓል በሚያከብሩበት ጊዜ ከሁሉ ቀድሞ ወደ ቅዱስ መቃብር ለመግባት ለኢትዮጵያ ማኅበር አለቃ መብት እንደነበረው የክርስቲያን ማኅበሮች ሁሉ የተስማሙበት ሥርዓት ፤

፮ኛ/ ይህንኑ የክርስቲያን ማኅበሮች የተስማሙበትን ሥርዓት የመንግሥት ባለ ሥልጣኖች በሕግ መዝገብ ያጸደቁበት ውሳኔ ማስረጃ ከነክልሼው ይገኝ በታል ።

፯ኛ/ በ፲፰ኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ የቅዱሳት መካናት ነገር ባለው ተጠ ብቆ እንዲቆይ የሚወስን ከሡልጣን ማህሙድ ሁለተኛ የታወጀ እስታቲ ስኮ የተባለው ውሳኔ ማስረጃ ከነክልሼው ይገኝበታል ።

፰ኛ/ የግሪክና የአርመን ማኅበሮች የኢትዮጵያን ንብረት ከሥልጣናቸው ሥር ስለማድረግ ባደረጉት ክርክር የኢትዮጵያ ይዞታ የነበሩትን ቦታዎችና ሥፍራ ለማወቅ የሚያስችል የሡልጣን ማህሙድ ከአንደኛ ውሳኔ ማስረጃ ከነክልሼው ይገኝበታል ።

፱ኛ/ እንደ አውሮፓ አቈጣጠር ከ፲፱፻፶፪ እስከ ፲፱፻፷፩ ዓ. ም. ስለ ዴር ሥል ጣን ገዳም ርስት ከግብፆች ጋር ስንከራከር ያደረግነው ረጅም ሙግትና የጆርዳን መንግሥት የሰጠን ውሳኔ (ፍርድ) ሆኖ እስከ መጨረሻው ያደ ረግነው ክርክር በሙሉ ተጽፎ ይገኛል ።

ስለዚህ ጽሑፉን ተመልክታችሁ በኢየሩሳሌም ያላችሁን መልካም ታሪክ እንድትረዱ ትጠራላችሁ ። (ተጋብዛችኋል)

## የእምነትና የጸሎት ግንኙነት ።

፩/ ከዚህ በላይ በተጻፉት ክፍሎች እንደ ተነገረው ፤ ኢትዮጵያ የመንግሥ ትና የእምነትም ሥነ ሥርዓት ያገኘችው ከኢየሩሳሌም መሆኑን የብሉይና የሐ ዲስ ኪዳንንም መሠረት በማድረግ የጠቀስኳቸው ማስረጃዎች ተመልካችን ሁሉ እንደሚያስደስቱ አምናለሁ ።

፪/ አሁንም ለኢትዮጵያ ሀገራችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእነሱ እንዲወለድ ተስፋ ከተነገረለት ከአብርሃም ዘር ከነገደ ይሁዳ ትውልድ ያላት የታሪክ ቅርስ ኢትዮጵያዊን ሁሉ የሚያኮራና ደስ የሚያሰኝ እንደ መሆኑ ፤ እንደዚሁም ደግሞ ከኢየሩሳሌም ጋራ ያላት የእምነትና የጸሎት የመሥዋዕት ግንኙነቷም ይበልጥ የሚያስደስት ነው ።

፫/ ኢየሩሳሌም ምዕራገ ጸሎት ምዕራገ መሥዋዕትም ናት ፤ ማስረጃ ለኖኅ በጥፋት ውሃ ፍጻሜ ከመርከብ እንደ ወጣ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት እንዳቀረበና እግዚአብሔርም ያቀረበውን መሥዋዕት ተቀብሎ ዘርህን ሁሉ



ዳግመኛ በጥፋት ውሃ አላጠፋም ብሎ ቃል ኪዳን እንደገባለትና የይቅርታው ንም ምልክት ይሁንህ ብሎ ቀስተ ደመናን የምሕረት ዓላማ (ባንዲራ) እንደ ሰጠው እናገኛለን ። ዘፍ ፱ ፡ ፩—፲፯ ።

፬/ ለአብርሃምም እግዚአብሔር አንድ ልጅህን ከተራራ ወስደህ ሠዋልኝ ባለው ጊዜ አብርሃም የእግዚአብሔርን ቃል ለመፈጸም ላንድ ልጁ ስንኳ ሳይ ራራ እንደሚታረድ በግ እጅና እግሩን አሥሮ ለማረድ ባጋደመው ጊዜ እግዚ አብሔር የልቡን መሥዋዕት ተቀብሎ አንዱን ልጅህንም አልከለከልህምና በእ ውነት በረከትን እባርክሃለሁ ፤ ዘርህንም እንደ ሰማይ ከዋክብትና በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋም አበዛዋለሁ ብሎ እንደ ባረከውና በራሱም እንደ ማለለት እናገ ኛለን ። ዘፍ ፳፪ ፩—፲፭—፲፯ ።

፭/ ሙሴም እግዚአብሔር እንዳዘዘው ከናንተ ዘንድ የልብ ፈቃድ ያለው የእግዚአብሔርን ቊርባን ያምጣ ብሎ እሥራኤልን እንዳዘዘ እናገኛለን ። ዘፀ አት ፴፭ ፬—፭ ። ስለዚህ የሙሴን እምነት የተቀበለ ሰው ሁሉም በዚህ ትእ ዛዝ መሠረት በያመቱ በኢየሩሳሌም መቅደስ እየተገኘ መባውን እንዲያቀርብ በሕጉ ይገደድ ነበር ።

፮/ አገራችን ኢትዮጵያም በሰሎሞን ልጅ በቀዳማዊ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዘመን የሙሴን ጽላትና የኦሪቱን ትእዛዛት ከተቀበለችበት ጊዜ ጀምሮ የብሉይን ሕግ ለማክበር ሰው ትልክ ነበርና ከዚያ ሲያያዝ በመጣው ልማድ ከኢትዮጵያ በዓሉን ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም የመጣው ኢትዮጵያዊ ሰው መባውን ከፍሎ በዓሉን አክብሮ ወዳገሩ ለመመለስ በሠረገላው ተቀምጦ ትንቢተ ኢሳይያስን እያነበበ ሲጓዝ ትንቢቱ በተፈጸመለት ጊዜ አጋጥሞት ኖሮ ከክርስቶስ ሐዋርያት አንዱ ፊልጶስ በወንጌል አሳምኖ በኢየሩሳሌም አውራጃ እንዳጠመቀው ከላይ በ፪ኛው ክፍል በ፯ኛው ቊጥር ከነጥቅሱ አስረድቻለሁ ።

## ኢትዮጵያ በሐዲስ ኪዳን ።

፯/ ኢትዮጵያ ሃይማኖተ ወንጌልን ከተቀበለች በኋላም ባራተኛው መቶ ዘመን ፍሬምናጦስን ወደ ግብፅ ልካ አባ ሰላማ በሚል ስያሜ ከአባ አትናቴ ዎስ ከእስክንድርያ ፓትሪያርክ የጳጳስነትን ሥልጣን ተቀብሎ በኢትዮጵያ ወን ጌልን ባስተማረ ጊዜ የኢትዮጵያ ምእመናን የክርስቶስን ሃይማኖት እንደ ተቀ በሉ በክርስቶስ ፍቅር የሱዳንንና የግብፅን በረሃ እያቋረጡ ክርስቶስ ለሰው ቤዛ መሥዋዕት ወደ ሆነበት ወደ ኢየሩሳሌም እየሔዱ ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ በቀደሰው ሥፍራ ሁሉ ገዳም አቅንተው የማኅበራዊ ኑሮ ሥራት መሥርተው በቀደምትነት እግዚአብሔርን በጸሎት በቊርባን እያገለገሉ የመኖራቸውን ቅድ ሚያ ይኸው የምጽፈው ታሪክ ዋና መረጃ ይሆናችኋል ።

www.ethiopianorthodox.org



ይህን «ኢየሩሳሌምን ዕወቁ» በሚል ርእስ ደርሰው ፤ አዘጋጅተውና
አሳትመው ያቀረቡት ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ እኚህ ናቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

181500

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም መካናት
ስላላት መብት ።

## ሦስተኛ ክፍል መጽሐፍ ።

ስለ ዴር ሥልጣን ገዳም ከኮፕቶች ጋር ስላለው የርስት መብት ክርክር የተነገሩ የሙግት ቃላትና ጥቂቶች ካሁን ቀደም ያልታተሙ የኢትዮጵያን ማኅበር ቀደምትነት የሚመሰክሩ ማስረጃዎች ከነክልሺያቸው የሚገኙበት ሆኖ

ከብፁዕ አባ ፊልጶስ
በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት
ቤተ ክርስቲያን
ሊቀ ጳጳስ
ትጋት ተዘጋጅቶ ታተመ ።

፲፱፻፵፬ ዓ. ም. ፲፫፻፸፪ ሂጅራ

## መ ግ ቢ ያ ።

በ፲፱፻፵፬ ዓ. ም. እንደ ኤሮፓ ዘመን አቈጣጠር በእንግሊዝኛ
የታተመው መጽሐፍ ትርጉም ።

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ገዳም በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ውስጥ ስላላት (የርስት) መብት ታሪክ እ-ኤ-አ በ፲፱፻፵፱ ዓ. ም. አሳትመን ባወጣነው መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱ አሥራ ስድስት አስረጂ ሰነዶች አብረው ታትመው ወጥተዋል ። ይሁን እንጂ በዚያን ጊዜ በጽሑፉ የበቃ ሥፍራ ካለመገኘቱ የተነሣ የክርክራችን ሁኔታ ለሕዝብ በቂ ሆኖ ተብራርቶ እንዲወጣና እንዲታወቅ ለማድረግ ሳይቻለን ቀርቶ ነበር ።

አሁን ግን ይህን መጽሐፍ እንዲታተም ስናደርግ ዋናው ሐሳባችንና ዓላማችንም የነገሮችን አመጣጥ ትክክለኛ ተራ እንዲይዙ ለማድረግና ይኸም ሲሆን ፤ በተለይ ታሪክንና ማናቸውንም ታሪካዊ ድርጊት ሁሉ በእውነትና በትክክል ለመመስከር ከመፈለጋችንም በላይ ለዮርዳኖስ (ለጆርዳን) ሐሺሚታዊ መንግሥት ሕዝብ እንዲሁም ከዚህ ግዛት ውጭ ለሚገኙ ለተቀሩትም ሁሉ ዴር ኤልሡልጣን በሚል ስያሜ ሲታወቅ የኖረው በኢየሩሳሌም የሚገኘው የኢትዮጵያ ገዳም ባሁኑ ጊዜ ክርክሩ የሚገኝበትን ሁኔታና ውጤት ትክክለኛና እውነተኛ መልኩን በመግለጥ እንዲታወቅ ለማድረግ ፈቃዳችን በመሆኑ ነው ። ስለክርክሩም ባደረግነው ገለጣ ሁሉ ያቀረብናቸውን ሐሳቦችና እንዲሁም የተጠቀሱትን ድርጊቶች ሁሉ በሙሉ የሚደግፉ ሕጋዊና ታሪካዊ የሆኑ ሰነዶች ስለሚገኙ አስፈላጊ መስሎ በታየን መጠን የእነዚህ አስረጂ ሰነዶች ፎቶስታቲክ ኮፒያቸው በእትሙ ውስጥ እንዲወጡ አድርገናል ።

www.ethiopianorthodox.org

በነገሩ አግባብ ወደ ነበራቸው የመንግሥት መ/ቤቶች ያቀረብናቸውን አንዳንድ ማሳሰቢያዎች (ማመልከቻዎች) ለመጀመሪያ ጊዜ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ታትመው እንዲወጡ አድርገናል ። እነዚህ ማሳሰቢያዎች የተላኩት እምነት ያሳደርንባቸውን አስረጂ ሰነዶች በመጥቀስ ስለሆነ ፤ ስለያንዳንዱ በተለይ አብራርቶ መጻፍ አስፈላጊ መስሎ አላገኘነውም ፤ ከነዚህም ውስጥ አብዛኛዎቹ ወንድሞቻችን ኮፕቶች አቅርበዋቸው ለነበሩት አስረጂ ሰነድና ማሳሰቢያዎች (ማመልከቻዎች) መልስ ክርክርና ትችት ሙግት ሁነው የቀረቡ ናቸው ።

እንዲሁም በተጨማሪ አንድ በ፲፱ ዙልሂጅ ፱፻፵፯ ሂጅራ ደግሞ በ፬ ጀማዲሉላ ፱፻፳፫ ሐጅራ የተጻፉ ሁለት ታሪካዊ የሆኑ የመንግሥት ሰነዶች አሁን ለመጀመሪያ ጊዜ ታትመው እንዲወጡ ስናደርግ በነዚህ ሁለት ሰነዶች ላይ በግልጽ መረዳት የሚቻለው በፋሲካ ትንሣኤ በዓላት ጊዜ በሚደረጉት ሥርዓተ ዑደቶች ላይ ገዳማችን ከተቀሩት ገዳማት ሁሉ የመጀመሪያውን የቅድሚያ (ማዕረግና ተራ) ይዞ ይገኝ እንደነበረ ነው ። «እሳት ወይም (ብርሃን) ከሚወጣበት ሥፍራ የቀዳሚት ሥዑር ዕለት በተቀዳሚ መግባት የሚችለው የኢትዮጵያውያን ገዳም አለቃ ነው ከርሱ ቀጥሎ ፓትሪያርኩ ሦስተኛ የአርመናውያን ገዳም አለቃ አራተኛ የጆርጂያውያን አለቃ አምስተኛ የሶርያውያን አለቃ ስድስተኛ የኮፕቶች አለቃ ነው ።

ይኸም የተራ አመዳደብ ከጥንት ጊዜያት አንስቶ የነበራቸውና ጽኑ የሆነ ልምድ ነው ። እነዚህ ሰነዶች ሌላ የሚያስከትሉት ትርጉምና ፍች ባይኖርም እንኳ በትክክል ሊያስረዱ የሚችሉት የኢትዮጵያ ገዳም በቅድስት ሀገር ውስጥ ከተቋቋሙት ከጥንታውያን ገዳማት አንድዋ እንደመሆንዋ መጠን የራሷን የግልዋ የሆኑ መንፈሳዊ ሥርዓቶቿን የምትፈጽምባቸው አያሌ ቦታዎች እንደ ነበሩዋት በግልጽ የሚያመለክቱ ናቸው ።

በዚህ ጉዳይ አግባብ የነበራቸው የዮርዳኖስ (የጆርዳን) ሐሺሚታዊ መንግሥት ባለሥልጣኖች መሥሪያ ቤቶች ዴር ሥልጣን በሚል ስያሜ በታወቀው የኢትዮጵያ ገዳም ላይ የተነሣውን ክርክር አሥር ዓመታት ያህል ጊዜ የፈጀ ረዥምና ጥንቁቅ የሆነ ጥናት አድርገው ስለነበረ በዚህም ጥናትና ምርምር በተገኘው ውጤት መሠረት በሰጡት ሚዛናዊ ፍርድ ላይ ሲወስኑ ፤ የዴር ሥልጣን ገዳምና የሚያዋስኑትን የአርባዕቱ እንስሳንና የቅዱስ ሚካኤልን ሁለት አብያተ ክርስቲያናት ጨምሮ የኢትዮጵያውያን ገዳም ርስትና ይዞታ መሆኑን ወስነው ነበር ፤ ይኸም ውሳኔ እንደ ኤውሮፓ አቈጣጠር ከየካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ. ም. በይፋ እንዲታወቅ ከተደረገ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ወንድሞቻችን ኮፕቶች ከስፍራው ላይና በጋዜጦችም ዓምድ ጭምር እጅግ ኃይለኛ የሆነ ጸብ አስነሡ ። ስለዚሁ ግጭት ከካይሮ ተልኮ የነበረው ሊቃነ ጳጳሳትና



የሕግ አዋቂዎች የሚገኙበት የኮፕቶች የመልእክተኛ ጓድ ማናቸውም መንፈሳዊና ጸሎተ ሥርዓት እንዳይፈጸም አግዶ ከዚያም በተጨማሪ ሲያስታውቅ (ስለ ክርክሩ) ኮፕቶች በጃቸው ይገኙ የነበሩትን አስረጅ ሰነዶች በሙሉ ሳያቀርቡ መቅረታቸውን በመግለጽ አመለከቱ ። ይህ አድራጎት እ- ኤ- አ- በየካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ. ም. የዮርዳኖስ መንግሥት በውሳኔ ያወጣውን ትእዛዝ እንዲቀዘቅዝና እንዲመክን ከማድረጉም በላይ የኮፕት ማኅበር ሌላ አዲስ አስረጂ እንዲያቀርብ ልዩ ልዩ አጋጣሚ ምክንያት ሊፈጥር ችሏል ፤ የዮርዳኖስ (የጆርዳን) መንግሥትም ስለሙግቱ ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት ይቻለው ዘንድ አስፈላጊ ሁኖ ስላገኘው በበኩላችን አስተያየታችንንና መከራከሪያችንን ለማቅረብ እንድንችል አዲስ የቀረቡትን አስረጂ ሰነዶች ትክክለኛ ግልባጭ እንዲደርሰን አደረገ ፤ ከዚያም ስለዚሁ መልስ እ-ኤ-አ- ግንቦት ፲፯ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ. ም. ጽፈን ያቀረብነውን ማሳሰቢያው (ማመልከቻ) በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ታትሞ እንዲወጣ አድርገናል ፤ ይሁን እንጂ የመጨረሻውን ውሳኔ አሁንም በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን ።

በተለይ አንባቢያችን አስተውሎ እንዲመለከተው የምንሻው የመተዳደሪያው ደንብ ወይም «እስታቱስኩዎ» የተባለው ሥርዓት አጀማመሩን ከዚያም ያገኘውን መስፋፋትና የደንቦቹንም ፍች ወይም ትርጉም እስከምን መጠን እንደደረሰ ስንል በማመልከቻችን ላይ በመጥቀስ የገለጽናቸውን ልዩ ልዩ ጥናቶችና ምርምሮችን ነው ።

በመጨረሻም ይህ ኃይለኛ ግጭት ያስነሣው ሙግትና ክርክር ከምን እንደደረሰና ያለበትንም ሁኔታ አንባቢው እንዲረዳውና እንዲነገዘበው ስንል ይህ የደከምንበት ተግባር ጠቃሚ ሳይሆን አይቀርም ብለን እንተማመናለን ። እውነተኛ ፍርድ አሸናፊ ሁኖ እንደሚወጣና በድል አድራጊነትም ጸንቶ እንደሚኖር እናምንበታለን ።

አባ ፊልጶስ

በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ

ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ

www.ethiopianorthodox.org

## አንደኛው ማስረጃ

ይህ ሰነድ የሚያመለክተው በቅዳሚ ሥዑር ቆሉት የክርስቲያን ማኅበሮች ወደ (መካነ ቅዱስ) መቃብሩ መቅደስ ሲገቡ የነበራቸውን የቅድሚያ ተራ ደንብ ነው ።

### ግልባጭ

ጉዳዩ ከዚህ በታች እንደተመለከተውና እንደተገለጸው ነው ። የገለበጠውም እጅግ መንፈሳዊና በሥነ ጽሑፍ አዋቂ በሆነው በተተኪነት የኢየሩሳሌም ገገር ልዑል እግዚአብሔር ሰላምንና በረከቱን በነቢዩና በርሱም ቤተ ሰብ ላይ ያወርድለት ዘንድ በተስፋ በምንመኝለት ። መለኪ. ዓሊ. ሐሰን አልቃዲ ፊርማ ዓሊ. ቢንሃሰን አልቃዲ ።

በሰማይ ጥበቃ ሥር በምትገኘው ኢየሩሳሌም ከተማ በሚገኘው የሸሪዓ ፍርድ ቤት የተመሰገነ ይሁን እንዲሁም እግዚአብሔር ነፍሱን ይማርና የኢ. ሩሳሌምና የአብርሃም አልከሊል (እብራይስጥ) ከተማ መምህር የነበረው የታላላቅ አዋቂዎች ክብር በሆነው ሃና ፊቱ ማውላና ሚሌት ናስርዴን ልጅ በሆነው በማውላና አልፊንድ ሻምሲዲን ፊት እጅግ የተከበሩና የተመሰገኑ ሰዎች ክብርና ሞገስ የሆነው የመለኪቱ ዓልዓለም ልጅ ቃዲ ሰዱዲን መሐመድ እና ቃዲሙሕያ ሻምሱዲን ሙሐመድ ቢን ሼይክ ባቀዲን አብደል ዋህብ ከኢ. ልማስሪ ልጆች አንዱ እንዲሁም እጅግ የተከበረው ሐሽም ናህ ላርጉት (?) እና ፋሪስ ቢን ሐጅአሊ. ቢንሃላስ ቀርበው እውነተኛና ሕጋዊ የሆነ አስረጅ ሰጥተዋል ፤ ጽሑፉም በትርጉም በአገላለጽ በይዞታ ሳይበላለጥና ሳይዛነፍ አንድ ሁኖ በተገኘው ቃላቸው ከጥንት ጊዜያት አንስቶ ከወረራውም ዘመን በፊትና (ከእስላም በፊት) ከዚያም በኋላ በኢየሩሳሌም የክርስቲያን ማኅበሮች በዓላት ባሁኑ ጊዜ የክርስቲያን ገዳማት ሁሉ ኢየሩሳሌም በሚገኘው መካነ ቅዱስ መቃብሩ (ቤተ ክርስቲያን) ውስጥ በአንድነት መሰብሰብ ልምድ እንደ ነበራቸውና እንዲሁም እነርሱ ብርሃን ብለው የሚጠሩት እሳቱ ከሚወጣበት ከመካነ ቅዱስ መቃብሩ ከጌታ መቃብር (ቤተ ክርስቲያን) ውስጥ ከሚገኘው ሥፍራ (ቦታ) መጀመሪያ በቅድሚያ ይገባ የነበረው የኢትዮጵያውያን (ሐበሾች) አለቃ ፤ ከርሱም ቀጥሎ ሁለተኛ የግሪክ ኦርቶዶክስ ፓትሪያርክ ፤ ሦስተኛ የአርመናውያን አለቃ ፤ አራተኛ የጆርጂያውያን አለቃ ፡ አምስተኛ የሶርያውያን አለቃ እና ስድስተኛ የኮፕቶች አለቃ ናቸው ፡ ይኸውም ተራ የክርስቲያን በዓላት በሆኑ ጊዜ ሁሉ በሕግ የሚቈጣጠሩትና የሚያከብሩት ልምዳቸው እንደነበርና በዚህም ፤ ምክንያት ፡ እየተሰበሰቡ ፡ አንድነት ሁነው ጧፎችን ያበራሉ ከላይ የተመለከቱት ባለሥልጣኖችና አለቆች የነበራቸው ተራ ፡ ይህ ስለነበረ ማንም ቢሆን በምንም ዓይነት ምክንያት ይህን ደንባቸውን የጠላና የተቃወማቸው አልነበረም ።

ስለዚህ ጉዳይ ቃዲው ታዞ የነበረው በ፲፱ ዙልሂጃህ ፱፻፵፯ ሐጅራ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

## የጉባኤው ምስክሮች ።

ትሑት አገልጋይ
ማህሙድ አሙኒ በዝበዘት
ሰርጀትን ኢብራሂም

አልሐጅ ኢብራሂም ተበጅ
አስፍ አልቃስጠ
ቢን አዱዊክ

ጸሐፊ
አህመድ ሂልሚ
ሽክ አህመድ ቢድ
አድድኽም
ሐጂ ሙራድ
ሰርጀንት ናሲፍ

ሌሎች በዚያው የነበሩ ናቸው ።

እንዲሁም ደግሞ እግዚአብሔር ምሕረት ይሰጠው ዘንድ የምንመኝለት የሃናፊቱ አልማውላና ስሩዲን ልጅ አልማውላ ሻምሱዲን በምስክርነቱ አጽድቆታል ።

## ሁለተኛ ማስረጃ ።

ይህ ሰነድ የክርስቲያን ገዳማት ማኅበሮች በቅዳሜ ሥዑር በዓል ዕለት ወደ መካነ ቅዱስ መቃብሩ ቤተ ክርስቲያን ለመግባት የነበራቸውን የተራ ማዕረግ ደንብ ትክክለኛ የፍርድ ውሳኔ የያዘና የሚያመለክት ነው ።

## ግ ል ባ ጭ ።

አብዱልራሀማን የኢየሩሳሌም ቃዲ ፤
(ፊርማ) ታማኙ አብዱራህማን ቢን ናሱህ
እግዚአብሔር (ፈቃዱ ሆኖ)

ይህ ሰነድ እንዲጻፍና እንዲዘጋጅ ምክንያት የሆነው በኢየሩሳሌም የተመሰገነው የሸሪዓ ፍርድ ቤት እግዚአብሔር ክብር ይስጠው እንዲሁም ሰላም በላዩ ላይ ይሰፍን ዘንድ የምንመኝለት ከዳኞች ሁሉ እጅግ የተመሰገነ ዳኛ የሕግ ትክክለኛ አስተርጓሚና የፍርዶች አስፈጻሚ ሕጋዊውንና ሕገ ወጥ ርኩሱን የሚለይ ችሮታው ክብሩና ከፍተኛው ሥልጣኑ ያለማቋረጥ ይቀጥል ዘንድ በምንመኝለት እንዲሁም በዚህ ዓለምና በላይኛውም ዓለም ያሉት ምኞቶች ሁሉ ይፈጸሙለት ዘንድ የምንመኝለት በዚህ ላይ ክንዱን አንተርሶ የፈረመበት የኢየሩሳሌምና አውራጃዋ የአብርሃም አልከሊል (እብራይስጥ) ከተማ ዳኛ የእስላም ዋና የፍርድ ሹም ፊት እንዲሁም የዓለም ኩራት በሆነው ኢየሩሳሌም ሲናን ሱብሺ (የፖሊስ ሹም) በተገኘበት በኢየሩሳሌም ያሉ የክርስቲያን ማኅበሮች ቀጥለው ባሉት ሰዎች አማካይነት እነዚህም አብዱል መሲሕ



www.ethiopianorthodox.org

ቢን ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያውያን (ሐበሾች) ማኅበር አለቃ ፤ ጀርማኖስ የግሪክ ኦርቶዶክስ ፓትሪያርክ ፤ እንድርያስ ቢን ኢብራሂም የአርመናውያን ማኅበር አለቃ ፤ ዩአቂም ቢን ዳውድ የጆርጅያውያን ማኅበር አለቃ ፤ አቡየቢድ ብንሀዲድ የሶሪያውያን ማኅበር አለቃ፤ ሚካኤል ቢን ዮሐና የኮፕት ማኅበር አለቃ፤ በነዚህ የማኅበር ወኪሎች መካከል አንድ ዓይነት ስምምነት እንዲደርስ ተደ ርጓል ፤ ከዚህ ቀን አንስቶ ለወደፊት በበዓላቸው ጊዜያት ውስጥ ከጥንት ዘመ ናት ጀምሮ ከወረራው ጊዜ በፊትና ከዚያም ወዲህ በልምድ ሲወርድ ሲዋረድ በመጣውና በተቀበሉትም መሠረት ማርት በተለይም በዝርዝር እነርሱ ብርሃን ብለው የሚጠሩት እሳት ከመካነ ቅዱስ መቃብሩ ቤተ ክርስቲያን በሚወጣ በት ጊዜ ኢየሩሳሌም በሚገኘው የጌታ መቃብር ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚ ሰበሰቡ ይሆናሉ ፤ እሳቱም ከሚወጣበት ሥፍራ ለመጀመሪያ በቅድሚያ የሚ ገባው የኢትዮጵያውያን አለቃ ፤ ከርሱም ቀጥሎ የግሪኩ ፓትሪያርክ ፤ በሦስተኛ የአርመናውያን ገዳም አለቃ ፤ አራተኛ የጆርጃውያን አለቃ ፤ አምስተኛ የሶሪ ያን አለቃ ፤ ስድስተኛ የኮፕቶች አለቃ ፤ ይሆናሉ ፤ ይህም የተራ ደንብ ምድብ ጥንታዊ የሆነ ልምዳቸው መሆኑ ነው ፤ በተጨማሪም አንድ ላይ በማኅበር ሆነው ከመንበረ ታቦቱ (?) አቀጣጥለው በማናቸውም ዓይነት ምክንያት በም ንም ዓይነት አኳኋን እርስ በርሳቸው ሳይጣሉና ሳይተናኮሉ አብረው የሚወጡ ይሆናሉ በዚህም ተስማምተውበታል ይህንን ደንብ ለመከተል ቃል ሲገቡ በሙሉ ፈቃድ በሙሉ ልብ አንዳችም ግዴታ ሳይኖርባቸው ነው ፤ ይህ ከሆነ በኋላ የዳኞቹ ሸንጎ ተበትኗል ።

ይህ ሰነድ ወጥቶ የነበረው በጅማ ዳሉላ ወር አራተኛው ቀን በ፱፻፳፫ ሃጅራ (እ. ኤ. አ. ፩ሺ፭፻፴፯) ዓ. ም. ነው ።

| | | |
|---|---|---|
| አልቃዲ | አልቃዲ | መንፈሳዊው |
| ታኪዮደን | ሙሐዩ አላዩቢ | አክባል አሊቢን ሳሌም |
| መሐመድ አቡ ሱዊይ | | ማውላና ሼክ |
| አሰቢታን | | ኢብደል ቃድር አልኮሉቲ |
| ሐጂ ሐመድ ኢርዷ | መውላና | ጸሐፊው |
| ቢን ሁሴን | ታርኪቲ | መሐመድ አልአዩቢ |





ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ የዴር ሥልጣንን ጉዳይ ለግርማዊ ንጉሥ ሑሴን ሲያመለክቱ ።

ግርማዊ ንጉሥ ሑሴን የስልምና እምነት መሥራች ከሆኑት ከነቢይ መሐመድ ዘር ዛሬ ዓረቢ ሳዑዲያ ከተባለው ከመካ ክፍለ ሀገር ሼሪፍ እየተባሉ ከኖሩት ከነ ቢይ መሐመድ ዘሮች ናቸው ። በመጀመሪያው የዓለም ጦርነት የቱርክን መንግሥት ከመካከለኛው ምሥራቅ ለማስለቀቅ የምዕራብ መንግሥታት ባደረጉት ጦርነት ጊዜ ከዓረብ የመካ ክፍለ ሀገር ባለሥልጣን የነበሩት ሼሪፍ ሑሴን በጦርነቱ ተካ ፋይ ስለነበሩ በጦርነት ፍጻሜ ሀገር ሲከፈል በዮርዳኖስ ምሥራቅ የዓሞን ክፍለ ሀገር ተሰጥቷቸው በዮርዳኖስ ማዶ ዓማንን ዋና ከተማ አድርገው በስመ ነገዳቸው የሐሺማይትን መንግሥት መሥርተዋል፤ሼሪፍ ሑሴን እንደሞቱም ታላቁ ልጃቸው ዓሚር ዓብደላ በዚሁ በዓማን ከተማ ንጉሥ ዓብደላ ተብለው ነግሠዋል ። በሼሪፍ ሑሴን ለተመሠረተው ለሐሺማይት መንግሥት ግርማዊ ንጉሥ ሑሴን የንጉሥ ተላል ልጅ ሦስተኛ ንጉሥ ናቸው ፤ ከላይ ከነቢይ መሐመድ የሐበሻን ውለታ መልሱ የሚል ንግር ስላለ ኢትዮጵያን በጣም የሚያከብሩ ዘሮች ናቸው ።



www.ethiopianorthodox.org

እንዲሁም ደግሞ የኢትዮጵያውያን ማኅበርም በበኩሉ ግልባጮቹ እንዲደር ሱት ከተደረገ ወዲህ አጥንቶ የመከላከያ መልሱን እስከሚያቀርብ ጊዜ ድረስ የዚህ ገዳም ጠቅላላ ይዞታና ሁኔታ የመተዳደሪያው ደንብ «እስታቱስኩዎ» ከመወሰኑ በፊት እንደ ነበረበት እንዲሆን ተመልሶ እንዲረጋ ተደርጓል ። ስለዚህ የኢትዮጵያውያን ገዳም በቁልፎቹ መክፈቻ ይጠቀም የነበረበትን መብት በመቈጣጠር በነዚህ መክፈቻዎች መጠቀም የሚችለው ይህ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት እንደ ነበረው ልክ ሁኖ እንዲሁም የመተዳደሪያውን ደንብ (እስታቱስ ኩዎ) መሠረት እያደረገ የኢየሩሳሌም አገረ ገዢ በየጊዜው ሊሰጥ የሚችለውን ደንቦች በመከተልና በመፈጸም መሆኑን እንዲያውቁት እየለመንን ፤ ከነዚህ ደን ቦች ውጪ ትእዛዝ በመጣስና በማናቸውም ሌላ ዓይነት መንገድ በቁልፎች መክፈቻ ለመጠቀም ሙከራ ቢደረግ ግን ይህ ክርክር የመጨረሻ ውሳኔ እስካ ገኘ ድረስ የቁልፎቹ መክፈቻዎች ተወስደው በመንግሥት እጅ እንዲቆዩ የሚ ደረግ መሆኑን አስታውቃለሁ ።

ይኸን ውሳኔ ሳስተላልፍልዎ በጉዳዩ አግባብ ካላቸው የመንግሥት ባለሥ ልጣኖች ጋር በመግባባትና በመተባበር በሁለቱም የገዳም ማኅበሮች መካከል ያለው ግንኙነት እንዳይደፈርስ በመጣጣር በፍጹም ወዳጅነት እንዲቀጥል ለማ ድረግ በተቻለ መጠን እንደምትደክሙበት ሙሉ እምነት ያለኝ መሆኔን እየገ ለጽኩ ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከዚህ በፊት እንደተለመደው ሁሉ መንግሥት ራሱ ከናንተ ጋራ የሚኖረው ማናቸውም ዓይነት ግንኙነት ሁሉ ፍጹም ልባዊ እንደሚሆንና ለሁሉም ተስማሚ የሆነውን መንገድ በመሻት በበጎ ፈቃደኛነ ትና ያላንዳች አድልዎ በትክክለኛ የፍርድ ሚዛን ላይ የተመሠረተ ሁኖ እንደ ሚያገኙት አረጋግጥልዎታለሁ ።

አክባሪዎ
ኢሕሳን ሐሽም ።

ግልባጭ ፩/ ለክቡር የአገር ግዛት ሚኒስትር
፪/ ለክቡር የንጉሣዊ ግቢ ሚኒስትር
ይኸን ጉዳይ እንዲመረምር ለታዘዘው ልዩ ጉባኤ ሊቀ መንበር እንደ መሆናቸው ፤
፫/ ለኢየሩሳሌም አውራጃ ገገር እንዲያውቁትና ትእዛዙን እንዲያ ስፈጽሙ ።

ውሳኔዎቹ ስለ መታገዳቸው ለተጻፈው ደብዳቤ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ የሰጡት መልስ ።

አባ ፊልጶስ
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ
የስልክ ቍጥር ፪፪፵፰ — የፖስታ ሣ. ቍ. ፳፭
ኢየሩሳሌም ፤



እ. ኤ. አ. ሚያዝያ ፪ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ. ም.
ለክቡር የኢየሩሳሌም ገዢ
ኢ የ ሩ ሳ ሌ ም ፤

ሰላምታችንን እያቀረብን እ. ኤ. አ. ሚያዝያ ፩ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ. ም. በቍ ጥር ፳/፵፱/፲፰፻፸፫ ላስተላለፉልን ደብዳቤ የሚከተለውን መልስ እንሰጣለን ።

፩/ የዴር ሥልጣን ገዳምና በውስጡም ያሉት ይዞታዎች የኢትዮጵያው ያን ገዳም ርስት መሆናቸውን ዐውቆ የተከበረው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ጉባኤ የካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ. ም. ባደረገው ስብሰባ ያጸደቃቸው ውሳኔ ዎች ለጊዜው በሥራ እንዳይውሉ መታገዳቸውን ከላይ ባስተላለፉት ደብዳቤ ጠቅሰው አስታውቀዋል ።

፪/ ይህ ውሳኔ እንዳይሠራበት መደረጉን ክቡርነትዎ ሲያብራሩ ፤ የገዳሙ ሁኔታ የመተዳደሪያው ደንብ (እስታቱስኩዎ) ከመመሥረቱ በፊት ወደ ነበረ በት አኳኋን እንዲመለስ መደረጉ ነው በማለት ፈትቶታል ።

፫/ ይህ ከላይ የተሰጠው ትርጉም ከዚህ በፊት አስቀድሞ ተሰጥተው የነ በሩትን ውሳኔዎች ፍጹም መካድ ብሎ ከመፍታት በስተቀር በምንም ዓይነት መንገድ የውሳኔዎቹ ከሥራ መታገድ የስታቱስኮው ደንቦች ከመመሥረታቸው በፊት ወደ ነበረበት አስተዳደር መመለስ ነው ተብሎ ሊፈታና ሊተረጐም ባለ መቻሉ ነው ።

፬/ የካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ. ም. ተሰጥቶ የነበረው ውሳኔ ካለፈ እነሆ ፵ ቀኖች ሁነውታል ። በዚህም ጊዜ ውስጥ ገዳማችንንና እንዲሁም የገዳማችን ሀብት የሆኑትን ንብረቶች ተረክበን ለአያሌ ዘመናት ወና ሁነው ቀርተው የነ በሩትን አብያተ ክርስቲያናት በማዕዳት ብዙ ድካምና የገንዘብ ወጪም አድር ገናል ። ከዚህም በላይ ደግሞ መንፈሳዊ ጸሎተ ሥርዓታችንን ለመፈጸም የሚ ያስችሉንን ንዋየ ቅዱሳት አልባሳት የመሳሰሉትን ሁሉ ወደነዚህ አብያተ ክር ስቲያናት እንዲዛወሩም አድርገናል ።

፭/ ክቡርነትዎ እንደሚያውቀው ሁሉ ፤ ሥርዓተ ጸሎታችንን የምንፈጽም በት እስካሁን ድረስ አንድም ሌላ ቤተ ክርስቲያን ስለ ሌለን ፤ የዓቢይ ጾምንና የሕማማትን ሳምንት ሥርዓተ ቅዳሴና ጸሎት በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ለመፈጸም ተዘጋጅተንና አዘጋጅተንም እንገኛለን ።

፮/ እንዲሁም ደግሞ የግብፁ ቄስ ይኖርበት በነበረው ክፍል ውስጥ አንዳ ንድ አስፈላጊ የነበሩ የማደስ ሥራዎችን በመጀመራችን ዕቃዎቹም እንዲወጡ አድርገናል ።

፯/ ስለዚህ ይህ በድንገት ሳይታሰብ ውሳኔዎቹ ከሥራ እንዳይውሉ የሚ ከለክል ትእዛዝ መተላለፉ ፤ ከመቼውም ይልቅ አሁን አሠቃቂ በሆነ ሁኔታ ላይ ሊጥለን ችሏል ። በተለይም ከረዥም ጊዜ ምርመራና ጥናት በኋላ የሚኒስ

www.ethiopianorthodox.org

ትሮች ምክር ቤት ሰጥቶት የነበረው ውሳኔ እንዲህ በቀላሉና እጅግ ባጠረ ጊዜ ውስጥ የሚሠረዝ መሆኑን ከቶ ልናስበውና ልንጠረጥርም አንችልም ነበር ።

፰/ ባሁኑ ሰዓት የፋሲካን በዓል ለማክበር ሥርዓተ ቅዳሴና ጸሎት የምናደርግበት ቦታ ባለማግኘታችን አስቸጋሪ የሆነ ጊዜ በፊታችን ተደቅኖ ተገኝቷል ። ዳሩ ግን ካሁን ጀምረን ስለዚህ በዓል የነበረንን ማናቸውንም ዝግጅት እንዲቆምና እንዲሠረዝ ማድረጋችንን ለክቡርነትዎ እናመለክታለን ።

፱/ የኮፕት ኦርቶዶክሳዊ ማኅበር አዲስ አስረጂ ሰነዶችን በእርግጥ እንዲያቀርብ ያስቻለው ፤ መንግሥት ራሱ በቂ የሆነ ጊዜና አጋጣሚ እንዲያገኝ በማድረጉም ጭምር ስለሆነ ፤ የዚህ ሙግት በር እንደገና አዲስ እንዲከፈት መደረጉና አዲስ ሰነዶችም እንዲቀርቡ አጋጣሚና ዓይነተኛ ምክንያት መጠበቅ እንደእውነቱ ከሆነ የፍርድን ደንብና ሥርዓት የሚቃወም ነው ። በተለይም ገናለገና አዲስ የሚቀርቡ ሰነዶች ይኖራሉ ተብሎ የተሰጡት ውሳኔዎች እንዲታገዱ መደረጉ ፍጹም አሳዛኝና ሕገ ወጥ ተግባር ነው ።

፲/ የተከበረው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ጉባኤ በየካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ. ም. ሰጥቶት የነበረው ውሳኔ ስለ መካናት ቅዱሳት የወጣውን የመንግሥትን አዋጅ አንቀጽና ድንጋጌ መሠረት አድርጎ ስለ ነበረ ፤ በዚህ አዋጅ ደንብ ያሁኑ ውሳኔ እንደ መጨረሻ ታስቦ ዳግም ለክርክር እንዳይቀርብና ሊሠረዝም አይገባውም ነበር ።

፲፩/ እንዲሁም ደግሞ አዲስ ለቀረቡት ማስረጃዎች መልስ ለመስጠት ዕድልና ጊዜ እስካገኘን ድረስ ውሳኔዎቹ በሥራ እንዳሉ እንዲቆዩ ለማድረግ መንግሥት ይቻለው ነበር ።

፲፪/ በነገሩ ለሚያገባቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሁሉ ይህ ደብዳቤ ከሙሉ ቃላቶቹና ይዞቱ ጭምር በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲተላለፍ ያደርጉልን ዘንድ በማክበር እንለምናለን ።

አክባሪዎ
አባ ፊልጶስ
በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት
ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ።

## ልዩ ልዩ ማሳሰቢያዎች ።

የዴር ሥልጣን ገዳም ከጥንት ጀምሮ የኢትዮጵያውያን መነኮሳት ርስት መሆኑን የሚመሰክሩ አያሌ ሰነዶች መኖራቸውንና የርስትነቱንም ታሪክ በመግለጽ የተዘጋጁ ማሳሰቢያዎች ሲሆኑ ፤ እያንዳንዳቸው ለዮርዳኖስ መንግሥት እንዲቀርቡ አድርገናል ።



## የመጀመሪያው ማሳሰቢያ ፤ ( ማመልከቻ )

### በኢየሩሳሌም ቅዱሳት መካናት ላይ ለኢትዮጵያውያን ገዳም ስላለው መብት ።

መግቢያ ፤ በዚህ ጉዳይ ከመናገራችን በፊት በቅድሚያ ማወቅ የሚገባን በፖለስታይን አገር ውስጥ ልዩ ልዩ የሆኑ የቤተ ክርስቲያንና የገዳማት ማኅበሮች በርስትነት ይዞታ የያዙዋቸው ቦታዎች ሁሉ የሚተዳደሩት «እስታቱስኩዎ» ወይም ባለው ይርጋ ሁኔታ በሚያስገድደው የአስተዳደር ደንብ ሥነ ሥርዓት ሊመሠረትና ሊገኝ የቻለው በነዚሁ መካናት ቅዱሳት ላይ የክርስቲያን ማኅበሮች መቋቋም ከጀመሩበት ጊዜ አንሥቶ ሲሆን ፤ ከዚያም በጊዜና በዘመን ብዛት የተገኙትን ልምዶችና ሥርዓቶች በመከተል ተከብሮና ተጠብቆ ሊኖር ችሎ ነበር ። ዳሩ ግን ለአያሌ ዘመናት ያህል ሲኖር የቆየ ሥርዓት እንደ መሆኑ መጠን በዚሁ ልክ ሰፊ የሆነ መስፋፋትን ከማግኘቱም በላይ አሁን በምንገኝበት ዘመን ወቅት እጅግ የተወሳሰበ መልክ ይዞ እንዲገኝ አድርጎታል በተለይም እስከዚህ ሁኔታ ድረስ እንዲደርስ ያደረገው የኦቶማን መንግሥት ሲሆን ይኸም የውጪ መንግሥታትን የፖለቲካ ጭነት አሸናፊ ሆኖ ባለመገኘቱ ካንዱ ሁለቱ ሳይባል በብዙ አጋጣሚ ጊዜ ውስጥ እርስ በርስ የማይስማሙና የሚጋጩ ንጉሣዊ አዋጆች ( ፊርማን ) እና ድንጋጌዎች አውጥቶ በማሰማቱ ነው ። በዚህ አኳኋን የኃይለኛ መንግሥት ጥገኞች ጥበቃ ሥር ሁነው ያልተገኙትና ኃይለኛም የሆነ የፖለቲካ ድጋፍ ያልነበራቸው የክርስቲያን ማኅበሮች አብዛኞዎቹ መብታቸው እንዲቀነስ ምክንያት በመሆኑ በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም የነበራቸውን ርስትና ንብረት ተቀምቶ እስከ ማጣት ደርሰዋል ። ከነዚህም ከተጎዱት የክርስቲያን ማኅበሮች መካከል አንድ የኢትዮጵያውያን ገዳም በተለይ መጠቀስ ይገባዋል ። እነዚህ ሁሉ ድርጊቶች እውነትና እርግጠኛ ለመሆናቸው ምስክር የሚያሻ ከሆነ ፤ በ፲፱ኛው ዘመን ገደማ በኢየሩሳሌም የታላቅዋ ብሪታንያ ቆንሲል የነበረው ሚስተር ዠምስ ፊን የጻፈውን ሚሞሪ መመልከት በቂ ይሆናል ።

## ኢትዮጵያውያኖች በኢየሩሳሌም ።

የዑማር ቃል ኪዳን ተብሎ በሚታወቀው አዋጅ የተመለከትን እንደ ሆነ በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ከተመሠረቱት ጥንታውያን የክርስቲያን ገዳማት መካከል የኢትዮጵያ ገዳም አንድዋ እንደ ነበረች ተጽፎ እናገኛለን ። ይኸም የዑማር ቃል ኪዳን ለኢየሩሳሌም ሕዝብ ታውጆ የነበረው የተከበረው የነቢዩ ወዳጅ የአማኞቹ አዛዥ አምላክ በሱ ይደሰት ዘንድ በምንመኝለት ዑማር ኢብን አልከጣብ በድል አድራጊነት ኢየሩሳሌም በገባበት ዘመን መሆኑ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

እንደሚለውም ከመልካም ምኞትና ሰላምታዎች አገላለጽ በኋላ ይህ ከኔ ከዑማር ኢብን አልኸጣብ የተሰጠ ቃል ኪዳን ነው ። (ሕጋዊ ውል) ሰላምና ፀጥታ ያገኙበት ዘንድ ፤--- ሕይወታቸው ከነአብያተ ክርስቲያናቸው ፤ መኖሪያ ቤቶቻቸው በይዞታቸው ውስጥ ካሉት ከሚቈጣጠሩዋቸው የመሳለሚያ ቅዱሳት መካኖቻቸው በኢየሩሳሌም ውስጥ ሆነ በውጪ ፤ እንዲሁም የመካነ ቅዱስ መቃብሩ ቤተ ክርስቲያንና የቤተ ልሔም ቤተ ክርስቲያን---የተቀሩት ም በዚያ የሚኖሩ ክርስቲያናዊ ዜጎች ማለት ጆርጇውያን ኢትዮጵያውያን ፤ እንዲሁም ለመሳለም ለሚመጡት ፈረንጆች ኮፕቶች አርመኖች ንስጥሮሳውያን ያዕቆባውያን ማሮናውያን ።

በእስላም ታሪክ ውስጥ ለሙቼውም ጊዜ እየተጠቀሰ የሚኖረው ይህ አስረጂ የሚጠይቅና የሚያሻው ታሪካዊ የሆነ የቃል ኪዳን አዋጅ ሌሎች ክርስቲያናዊ ዜጎች ለጉብኝትና ለመሳለም ብቻ ይመጡ ከነበሩበት ዘመን አስቀድሞ በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ተመሥርተው ከተቋቋሙት ገዳማት የኢትዮጵያ ገዳም አንድዋ እንደ ነበረች በማያጠራጥር አኳኋን አብራርቶና አጉልቶ የሚያሳይ ነው ። ስለዚህ በነዋሪነት በተመሠረተ ማኅበር መካከልና አልፎ አልፎ ባንዳንድ አጋጣሚ ምክንያት ቅዱሳት መካናትን ለመሳለም ብቻ ከሚመጣ ማኅበር ጋር ያለውንና ሊኖር የሚችለውንም የመብት ልዩነት ለመረዳት አስቸጋሪ አይሆንም ።

ሡልጣን ሰሊም ፤

ይኸ ከላይ የተገለጸው አስተያየት ድጋፍና አስረጂ የሚያሻው መስሎ አይታየንም ። ዳሩ ግን አስፈላጊ ሁኖ ቢገኝም ፤ የኦቶማን መንግሥት በድል አድራጊነት በኢየሩሳሌም ሡፍሮ ገገር በነበረበት ጊዜ በ፱፻፳፫ ሂጅራ ወይም እ. ኤ. አ. በ፲፭፻፲፯ ዓ. ም. የሡልጣን ሰሊም አዋጅ በመባል የታወቀውን የመጀመሪያ ንጉሣዊ ትእዛዝ መመልከቱ ብቻ በቂ ሊሆን ይችላል ። ይህንንም አዋጅ ከዚህ ጋር በማያያዝ እያቀረብን (በጀርባው ቍ/ ተመልከት) በዚህ ታሪካዊ የሆነ ትእዛዝ ላይ እንደተመለከተው የኢትዮጵያ ገዳም በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም መካናት ቅዱሳት ላይ እጅግ የተለየ መብትና አስተያየት እንደ ነበራት ከመግለጹም በላይ ፤ በተለይ ጽሑፌ ሲያስረዳ ፤ የጌታን መቃብር ቤተ ክርስቲያንን አልፎ የሚገኘው ዴር ሥልጣን ያሉትን ክፍሎችና መኖሪያ ቤቶች ጨምሮ በሙሉ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያውያን ገዳም ሀብትና ይዞታ እንደ ነበረ ይመሰክራል ።

## በ፩ሺ፺፰ ሂጅራ የተጻፈ ሰነድ ።

ይኸን ሰነድ የኮፕት ኦርቶዶክሳዊት ማኅበር ክርክራቸውን ከመቃወም ይልቅ ይደገፉል ብለው የሚያምኑበት ነው ። ይሁን እንጂ በሱ ላይ ከመናገራችን አስቀድሞ በኢየሩሳሌም የሚገኘው የኢትዮጵያ ገዳም በዚያን ዘመን



ውስጥ በኢኮኖሚ በፖለቲካና በሃይማኖት ይገኝ የነበረበትን ሁኔታ ከብዙ በጥቂቱ ማብራራት ሳያሻ አይቀርም።በኢትዮጵያ የነበረው የአገዛዝና የመንግሥቱ ሁኔታ ፍጹም የተረጋጋ ሁኖ ባለመገኘቱ ገገርዎቹም እርስ በርሳቸው ያልተስማሙ ብኩኖችና ሥርዓት ያጡ በመሆናቸው በዚህ ዓይነተኛ ምክንያት ተፈላጊውን ርዳታና ድጋፍ ለማግኘት ባለመቻሉ በኢየሩሳሌም የሚገኘው የኢትዮጵያ ገዳም እጅግ አድርጎ ድኅነት ከተጫናቸውና ከመጠን በላይ ከተዳከሙት ማኅበሮች መካከል አንድዋ ስለነበረች የዕለት እንጀራ እስከ ማጣት ደርሳ እንደ ነበረች ይታወቃል ። ከዚህም በላይ ደግሞ ያንድ ኃይለኛ መንግሥት ፖለቲካዊ ድጋፍ ስላልነበራትና እንዲሁም አብዛኛዎቹ መነኮሳት የአገሩን ቋንቋ ንግግር በፍጹም የማያውቁ ስለነበሩ እነዚህን በመሳሰሉ ልዩ ልዩ ምክንያቶች የኢትዮጵያ ገዳም ተጠቂና ደካማ እንድትሆን አድርጓት ነበር ። ስለ ሃይማኖት እምነት ስንኳ ሳይቀር የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የኮፕት ኦርቶዶክሳዊት ክርስቲያንን እምነት እንድትከተል ሁና በመገኘትዋ በዚህ አኳኋን የኮፕት ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያንን እምነት እንድትከተል ሁና በመገኘትዋ በዚህ አኳኋን የኮፕት ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን አለቆች በኢትዮጵያውያን ጳጳሳትና ቀሳውስት ለመቀባትና የመሾም ሥልጣን አብቅቷቸው ነበር ። ከዚህም አልፎ በኢትዮጵያ ከግዛትዋም ውጪ የነበራቸውን የገቢ ምንጭ ሳይቀር እስከ መቈጣጠር አብቅቷቸው ስለ ነበረ ፤ በዚያን ዘመን ታሪክ ውስጥ የኢትዮጵያ ገዳም «ክርስቲያናዊ» የኮፕቶች ክርስቲያን ገዳም እየተባለ እስከ መጠራት ደርሶ እንደ ነበረ ይታወቃል ። ይህም ሊሆን የቻለው በሃይማኖት እምነትም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ሥልጣን የኢትዮጵያውያን ገዳም የኮፕት ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያንን እንድትከተል በመገደድዋ ነው ። በዚህም አዋጅ ውስጥ የሚከተለው ተጽፎ ይገኛል ። «በኢየሩሳሌም ጥበቃ ሥር ሁነው በነበሩት ጥብቅ ክርስቲያኖች ተወስኖና ተከልሎ ( ? ) ከዚህ በፊት በዴር ሥልጣን ስም ይታወቅ የነበረው የኮፕት ክርስቲያናዊ ማኅበር ከታች ( ? ) ከተመለከተው ዘመን ቀደም ብሎ እንዲፈተሽ ሲደረግ-----» ዳሩ ግን ወደ ኋላ ተመልሰን የሡልጣን ሳሊምን ንጉሣዊ ትእዛዝ የተመለከትን እንደ ሆነ ይህ ሰነድ (በጀርባው ቍጥር ፩ ምልክት ተመልከት) የዴር ሡልጣን ገዳም የኢትዮጵያውያን መነኮሳት ገዳም ርስት መሆኑን በግልጽ የሚያስረዳና ከዚያም ወዲህ ደግሞ በ፩ሺ፭፻፶ ዓ. ም. ሡልጣን ሱሌይማን ይህንኑ በማጠንከር (በማጽደቅ) ፈርሞ ባወጣው ትእዛዝ ላይ እንዲጸና መደረጉ ይታወቃል ። አሁን ክርክር የሚደረግበት ሰነድ በ፲፯፻፹፯ ዓ. ም. የወጣ ሰነድ ነው ። እዚህ ላይ በቀጥታ ሊያስጠይቅ የሚችለው በ፲፭፻፶ ዓ. ም. እና ፲፯፻፹፯ ዓ. ም. ባሉት ዘመናት ውስጥ ምን ዓይነት ታሪካዊ ድርጊት እንደ ደረሰና የዴር ሡልጣን ገዳም ሀብትና ርስትነቱ ከኢትዮጵያውያን ወደ ኮፕት ኦርቶዶክሳዊት እንዴት ሊዛወር እንደ ቻለ ለማወቅ ነው ። ይኸንን የሚደግፍ በዘመኑ የተፈጠረ አንዳችም ታሪካዊ

www.ethiopianorthodox.org

ፈቃድ ሳይፈቀድ በመቅረቱም ነው።ነገር ግን ይህ የአፈላለግ ሁኔታ በዚህ ፍርድ ቤት መዝገብ ውስጥ እንዲፈቀድ ሲደረግ ከዚህ ጋር አባሪ አድርገን ያቀረብናቸው አስረጅ ሰነዶች ያን ጊዜ ተገኝተው ቢሆን ኖሮ የኮፕት ኦርቶዶክሳዊ ማኅበርና በነገሩም የሚያገባቸው የመንግሥት ባለሥልጣኖች ሁሉ ባልካዷቸውና በሌላ ልዩ ልዩ አዋጅና ትእዛዝ ባልተቃወሟቸው ነበር ። እዚህ ላይ ለመጥቀስ የምንሻው ባሮን ኖልዴ የተባለው የታሪክ ጸሐፊ እ.ኤ.አ. በ፲፱፻፺፫ ዓ.ም. ላይ በኢስታንቡል ከተማ በሚገኘው ቤተ መዛግብት ውስጥ የኦትማንን መንግሥት ሰነዶች እየመረመረ ባደረገው ልዩ ጥናት ላይ በመጨረሻ ውሳኔ ሲሰጥ እንዲህ ይላል «ዴር ሥልጣን የኢትዮጵያውያን መነኰሳት የተረጋገጠና ፍጹም የማያከራክር ርስታቸው ለመሆኑ በበኩሌ አያጠራጥረኝም ይህንንም በግልጽ ለመረዳት እ.ኤ.አ. ፲፰፻፵፬ና ፲፰፻፺፩ ዓ. ም. መካከል የተሰጡትን አዋጅና ትእዛዞች ከመጽናታቸው በጣም አስቀድሞ ወጥተው በነበሩበት ትእዛዝና ድንጋጌዎች የተመሰከረና የተረጋገጠ ሆኖ ስለሚገኝ መብትና ርስትነቱ ፍጹም የራሳቸው የሆነና ከላይ ከተጠቀሰው የዴር ሥልጣን ገዳም ጋር ተያይዘው ያሉትም አብያተ ክርስቲያናት ጭምር የግላቸው በመሆኑ የነዚህን ሥፍራዎች ቁልፍ መክፈቻ መያዝ በመብት እንደሚገባቸው በግልጽ የታወቀ ነው (?) በ፲፰፻፵፬ ዓ. ም. እና በ፲፰፻፺፩ ዓ. ም. በወጡት አዋጅና ትእዛዝ ላይ የኮፕት ኦርቶዶክሳዊ ማኅበር ክርክሩን ይደግፋል ብሎ የሚያምንባቸው መሆናቸው ነው ። ስለዚህ ባሮን ኖልዴ በዓለም ላሉት ከታላላቅ የሕግ አዋቂዎች አንዱ እንደመሆኑ መጠን ረቂቅ ከሆነ ምርምርና ጥናት በኋላ እንዲህ በመሰለ ውሳኔ ላይ በመድረሱ ታላቅ ቁም ነገር የሚጣልበትና የተከበረም ሆኖ እናገኘዋለን ፤ ( ዲባይንስ የተባለውን የቅዱሳት መካናት መጽሐፍ ተመልከት )

ከዚህም አያይዘን በተጨማሪ በ፲፱፻፺፫ ዓ.ም. ላይ በመካናት ቅዱሳት ላይ ተነሥቶ የነበረውን የመብት ክርክር ለማዋየት ኢየሩሳሌም ገብቶ የነበረው ልዩ የኢንተርናሲዮናል መልእክተኛ ኮሚቴን ማስታወስ ይገባናል ይህም ኮሚቴ ከዚህ በታች የተመለከቱትን የልዩ ልዩ ክርስቲያናዊ ማኅበሮችና የቤተ ክርስቲያን አለቆች አንድ በአንድ አዳምጠ ።

፩ኛ. የግሪክ ኦርቶዶክሳዊ ፓትሪያርክ ፤
፪ኛ. የአርመናውያን ፓትሪያርክ ፤
፫ኛ. የላቲን ፓትሪያርክ ፤
፬ኛ. የአርመናውያን ካቶሊክ መንበረ ፓትሪያርክ ወኪል ፤

እነዚህ ሁሉ የቤተ ክርስቲያን አለቆች ዴር ሥልጣን የኢትዮጵያውያን መነኮሳት ርስትና ንብረት መሆኑን መስክረው አረጋግጠዋል ፤ ይህንንም ለመረ



ዳት ከተፈለገ ከላይ በተመለከተው መንበረ ፓትረያርኮች ውስጥ በኃላፊነት የሚገኙትን ሰዎች በቤተ መዛግብታቸው የሚገኙትን ፋይሎችና ማኅደሮች ከፍተው አስረጂዎቹን እንዲያቀርቡ በትእዛዝ መጠየቅ በቂ ሊሆን ይችላል ።

የኮፕት ኦርቶዶክሳዊ ማኅበር ባቀረበው ማሳሰቢያ (ማመልከቻ) ላይ እንደገለጸው የዴር ሥልጣን ገዳምን ለማደስ የሚያሻ ሆኖ በተገኘ ቍጥር ተጠያቂውን ሥራ ለመሥራት መብቱ እንደሆነ ይናገራል ፣ ይሁን እንጂ ከላይ የተመለከቱት መልክተኞች ክርክሩን በሚያጠኑበት ጊዜ የፓለስታይን አስተዳዳሪ መንግሥት ይህንኑ ጉዳይ አንሥቶ ስለነበረ በዚያን ጊዜ የኮፕት ኦርቶዶክሳዊ ማኅበር ይህ ይገባኛል የሚለውን መብት ለማስመስከር ሳይችል ቀርቷል ፤ እንዲሁም ደግሞ የኢትዮጵያውያን መነኮሳት የሚደግፋቸውን አስረጂ ሰነዶች ገና አላገኙም ነበርና በዚህ ምክንያት የኢንተርናሲዮናል ኮሚቴ በነበረው ሥልጣን ሲወስን በዴር ሥልጣን ገዳም ውስጥ ማናቸውንም የማደስ ሥራና ዛፎችን መመልመልና መከርከም ጭምር ሳይቀር በአስተዳዳሪው መንግሥት ኪሣራ እንዲሠራ ትእዛዝ ሰጥቶ በዚህ ጉዳይ የኮፕት ኦርቶዶክሳዊ ማኅበር ሁለተኛ እንዳይገባ ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል ።

## በበዓላት ጊዜ የዴር ሥልጣን ሰሜናዊ በር እንዲከፈት ስለ መደረጉ ።

በዴር ሥልጣን ቁልፍ ያላንዳች አግባብ የኮፕት ኦርቶዶክሳዊ ማኅበር እንዴት ሲጠቀምበት እንደ ነበርና በኢትዮጵያውያኖችም መካከል ገብቶ ስለ ፈጀው የተስቦ በሽታ ፤ እንዲሁም ግብፃዊው ኢብራሂም ፓሻ በኢየሩሳሌም በድል አድራጊነት በመግባቱ እነዚህን በመሳሰሉ ልዩ ልዩ አጋጣሚ ምክንያቶች ሊገኙ የተቻሉትን ሁኔታዎች ሁሉ ጠቅሰን ካስረዳን በኋላ ቁልፎቹ በእጃቸው በመገኘታቸው ይኸን እንደ ታላቅ ምክንያት በመቍጠር በበዓላት ጊዜ የገዳሙ በር እንዲከፈት ለማድረግ የኢትዮጵያውያን መነኮሳት እንዲለምኑዋቸውና እንዲለማመጧቸው ለማስገደድ ሲሉ ካደረጓቸው ሙከራዎች መልሳችንን በሚከተለው አረፍተ ነገሮች አጠቃለን እናቀርባለን ።

፩. የገዳሙ መክፈቻዎች በኮፕት ማኅበር እጅ መገኘታቸው የኢትዮጵያ ገዳም የነሱን ፈቃድ እንዲጠይቅ በመሠረቱ ሊገደድ አይገባውም ። ምክንያት ሊሆን የቻለው በመተዳደሪያው ደንብ በእስታቱስኮዎ አስቀድሞ ስለተወሰነና ይህም ደንብ ራሱ ከዚህ በላይ እንደ ገለጽነው ሁሉ ሕግንና ትክክለኛ ፍርድን የተከተለ ሁኖ ባለመገኘቱ ነው ።

፪. ይህ ጉዳይ ክርክሩን ይመለከትና ይመረምር የነበረው ልዩ ኮሚቴ መጥቶ በነበረበት ጊዜ ፍጹም ያልተነሣ ከመሆኑም በላይ በየጊዜው ከመስቀል በዓል ዋዜማ ጀምሮ የኮፕት ኦርቶዶክሳዊ ማኅበር በራሱ ፈቃድ በሮቹን መክፈት ልምድ እንደ ነበረው ይታወቃል ።

www.ethiopianorthodox.org

፪. ብፁዕ የኮፕት ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ አሁን ባቀረቡት ማስታወሻ ላይ ጽሑፋቸውን ሲጀምሩ የዴር ሥልጣን ስያሜ ሡልጣን የተባለው ቃል የተጨመረበትን ምክንያት አብራርተው ለመግለጽ ሞክረዋል ። ውሳኔያቸውንም በመቀጠል ኮፕቶች የመንግሥቱ ዜጎች እንደመሆናቸው መጠን በየጊዜው በሥልጣን ላይ ከነበሩት ሡልጣኖች ውስጥ አንዱ በስጦታ መልክ ያበረከተላቸው መሆኑን ይናገራሉ ። ይሁን እንጂ ይኸንን ገዳም ለኮፕት ማኅበር ያበረከተው ሡልጣን ማን እንደነበርና የተሰጠበትንም ዘመን ብፁዕነታቸው ለይተው አያረጋግጡም ። የሆነ ሆኖ ከኦቶማን መንግሥት ወረራ በፊትም እጅግ አስቀድሞ በነበሩት ዘመናት ሁሉ የዴር ሥልጣን ገዳም በዚሁ ስያሜ ብቻ ይታወቅ እንደነበር መዘንጋት የለበትም ።

በዚህ ባቀረቡት ማስታወሻ በመጀመሪያው ገጽ ፲ኛና ፲፩ኛ መሥመር ላይ የተመለከተው ሐሳብ አስተያየት ሳይደረግበት ሊታለፍ የሚገባ መስሎ አይታየንም ። ይኸውም ብፁዕ የኮፕት ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ በራሳቸው አነጋገር እንደ ገለጹትና ለማለት እንደፈለጉት « የኢየሩሳሌምን ቅዱሳት መካናት ግብፆች በየጊዜው መጐብኘት የጀመሩት ወንድሞቻችን ኢትዮጵያውያኖች የዚህን አገር መግቢያ ጥርጊያ መንገዱን ከማወቃቸው በፊት እጅግ አስቀድሞ ነው « ሲሉ ተናግረዋል ። ይህ መግለጫቸው ከእውነትም ሆነ ከታሪክ አስረጅ ጋር እጅግ የተራራቀ ሁኖ በመገኘቱ ለዚህም ሌላ የተሻለ ማስረጃ ለማግኘት ሳንርቅ ኢየሩሳሌም በዓረብ መንግሥት በተወረረችና በተያዘች ዘመን ውስጥ የታማኙ አዛዥ ኦማር ቢን አልኸታብ ለፓትሪያርክ ሰፍሮኒዮስ ሰጥቶት የነበረውን የቃል ኪዳን አዋጅ ማስታወስና መመልከት ይበቃል ፤ ይኸም የቃል ኪዳን አዋጁ በታሪክ እጅግ የገነነና የታወቀ ከመሆኑም በላይ በማናቸውም የዓረብን መንግሥት ዜና ታሪክ በሚጠቅስ ጽሑፍ ሁሉ ወጥቶ ይገኛል ። በዚህም ታሪካዊ የቃል ኪዳን አዋጅ እንደተገለጸው ቀጥሎ ያለውን እንጠቅሳለን «------ በዚያ ያሉ ማናቸውም የክርስቲያን ዜጎች እነዚህም ጆርጃውያን ፤ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም ለጉብኝት ( መሳለም ) የሚመጡት ፍራንኮች ፤ ኮፕቶች ፤ ሶርያውያኖች ፤ አርመናውያን አስትሮያውያን ፤ ያዕቆባውያን ፤ ማሮኒታውያን ----» እያለ ለይቶ በመጥቀስ የጻፈው አረፍተ ነገር ሌላ ተጨማሪ ፍችና ማብራሪያ የሚያስፈልገው ሁኖ አይገኝም ፤ በዚህ መሠረት እንግዲህ ከእስላም ወረራ በፊት አስቀድመው በነበሩት ዘመናት ሁሉ ኢትዮጵያውያን በኢየሩሳሌም ቅዱሳት መካናት አካባቢ ውስጥ ይኖሩ እንደነበረ የታወቀ ነው ፤ የቀሩት ማኅበሮችና በተለይም የኮፕት ገዳም ማኅበር ምእመናን ኢየሩሳሌም ለጉብኝት ብቻ በሚመጡበት ወቅት የኢትዮጵያ ገዳም ማኅበር በዚያ ነባር ሁኖ ይቀመጥ ነበር ። ብፁዕ የኮፕት ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ላቀረቡዋቸው አስረጅዎች ይህ የኦማር ቃል ኪዳን አዋጅ እጅግ ኃይለኛ መቃወሚያ ይሆንባቸዋል ።



፫. ብፁዕ የኮፕት ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ በዚህ ማስታወሻቸው ገጽ ፪ ፫ኛ ፓራግራፍ ላይ ሲገልጹ የዴር ሥልጣን ገዳም እንግዶቻቸውን ለመቀበል አንድ ስሙ ካልታወቀ ሡልጣን በስጦታ የተበረከተላቸው በመሆኑ ለብዙ ዘመናት ያህል በኮፕት ማኅበር ቊጥጥር ሥር ሲተዳደር ቆይቷል ። ብለው ያረጋግጣሉ ፤ ይሁን እንጂ ብፁዕነታቸው ለዚህ ጉዳይ አስረጂ ብለው በማያያዝ ያቀረቡዋቸው ሰነዶች ሲመረመሩ ደግሞ የኮፕት ማኅበር የኢትዮጵያውያን መነኰሳት ከዴር ሥልጣን ገዳም እንዲባረሩ ከተደረገበት ዘመን ከ፲፰፻፹፰ ዓ. ም. ወዲያ አያልፍም ። በዚህ ዘመንና ዓመተ ምሕረት ውስጥም እንደሚታወሰው ሁሉ የመሐመድ ዓሊ ፓሻ ልጅ ኢብራሂም ፓሻ በድል አድራጊነት ኢየሩሳሌም የገባበት ዘመን ስለነበረ ኮፕቶችም ግብፆች በመሆናቸው ከኢየሩሳሌም መካናት ቅዱሳት አንድ አንድ ሥፍራዎች እንዲሰጣቸው የተደረገበት ዘመን ነው ። ነገር ግን ይህ የዴር ሥልጣን ገዳም ከጥንት ጊዜ አንስቶ የኮፕት ማኅበር ገዳም ቢሆን ኖሮ በታሪክ የተደገፈና የተመሰከረ ጥንታዊ ተብሎ ሊገመት የሚችል አንድ እንኳን ሰነድ ለማቅረብ ባልተሳናቸው ነበር ፤ ስለዚህ በኢትዮጵያውያን መነኰሳት እጅ የሚገኙት ሰነዶች ከነዚህ ጋር እንዲነጣጠሩ ሲደረግ እጅግ ጥንታዊ ሁነው ይገኛሉ ። አንዳንዶቹ እስከ ኦማር የቃል ኪዳን አዋጅ እወጣበት ዘመን ድረስና የተቀሩትም የኦቶማን መንግሥት ወረራ እስከጀመረበት ጊዜ ድረስ ርቀው እንደሚሔዱ ከዚህ በታች ለመግለጽ እንሞክራለን ።

፬. ብፁዕነታቸው በዚሁ ባቀረቡት ማስታወሻ ገጽ ፫ ፬ኛው ፓራግራፍ ላይ ደግሞ እንደተመለከተውና እንደገለጹት የኢትዮጵያውያንን ገዳም ሀብትና ንብረቶቹን ለማስተዳደርና ለመቈጣጠር በማለት በግሪክ ኦርቶዶክስና በአርመናውያን መካከል ታላቅ የሥልጣን መወዳደር ተነሥቶ ነበር በማለት ተናግረዋል ። ነገር ግን እንደ እውነቱ ለመናገር ከተፈለገ ይህ ስሜት በሁሉም ማኅበሮች ውስጥ የነበረና ኮፕቶች ሶርያውያኖች ከዚህ በታች እንደምንገልጸው አንዳንድ ማኅበሮች ጭምር እንደሚያደርጉት ሁሉ የግሪክ ኦርቶዶክስና የአርመን ማኅበርም የተቀሩትን ኦርቶዶክስ ማኅበሮች ንብረትና ሀብት በውስጣቸው ደርበው ለማስተዳደርና ለመቈጣጠር እርስ በርሳቸው ታላቅ የመሻማት ውድድር መኖሩን መደረጉ የተለመደ ተግባር ነበር ። በዚህም አኳኋን የኢትዮጵያውያን ገዳም ሀብትና ንብረት በጥበቃቸው ሥር እንዲሆን ለመደረግ በቅቷል ። ይሁን እንጂ ይህ ሁኔታ የርስት ባለቤትነትን ማዛወር ነው ተብሎ ሊፈታና ሊተረጐም ስለማይችል ፤ እንዲሁም ባንድ በኩል ደግሞ ይህ ሊሆን የቻለውም በዘመኑ ሥልጣን ላይ የነበረው አለቃ ባለሥልጣን አስፈላጊ መስሎ ስለታየው በሰጠው የትእዛዝ ውሳኔ ላይ ሁሉቱም ባለጉዳዮች በመጠኑ ያህል እንዲስማሙበት ከተደረገ በኋላ ነው ። በዚህ ዓይነት አኳኋን የተፈጸመ ስም ምንነት ላልተወሰነ ጊዜ ድረስ እንዲቆይ ቢደረግም ቅሉ በማናቸውም ዓይነት

www.ethiopianorthodox.org

ሕግ ወይም ድንጋጌ የርስት ባለቤትነትን እስከ ማዛወር ደረጃ ሊያደርሰው እንደማይችል የተረጋገጠ ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ በአደራ ጥበቃ ምክንያት ማንም ሰው ቢሆን በተቀበለው የአደራ ሀብትና ንብረት ላይ የባለቤትነት መብት ሊሰጠው ወይም ይገባኛል ሲል ሊጠይቅና ሊከራከር የሚያስችለው አንዳችም ዓይነት ሕጋዊ መንገድ ሊኖር በባለመቻሉ ነው ።

፳- የኮፕት ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ በማስታወሻቸው ገጽ ፬ ላይ ሚስተር ሐርቬይስ በጻፈው መጽሐፍ በፓለስታይን የጥንታዊ ዕቃዎች ሚዝዬም ዲረክተር የነበሩት ሚስተር ሬችሞንድ የሰጡትን የመግቢያ ርእሰ ቃላት በመጥቀስ የኢትዮጵያ ገዳም በኢየሩሳሌም መካናት ቅዱሳት ውስጥ በርከት ያሉ ቦታዎች እንደነበሩዋቸውና ነገር ግን ከ፩ሺ፯፻፰ ዓ. ም. ወዲህ ስለይዞታቸው የተጠየቁትን ግብርና አበል ለመክፈል ባለመቻላቸው ርስቶቻቸውን እንዲያጡ ሁነዋል በማለት ብፁዕነታቸው ወስነው ለማረጋገጥ ሞክረዋል ።

በዚህ በሰጡት ውሳኔ አረፍተ ነገር ውስጥ ስለ ተገለጸው አሳብ የምንሰጠው አስተያየት በተባለው መጽሐፍ መግቢያ ሚስተር ሪችሞንድ ስለ ገለጸው አሳብ አስረጅ መፈለግ መሞከር የክርክራችንን መንገድ የማይመለከትና የማይጠቅም ከመሆኑም በላይ ፤ በተለይ የምንሻው « የመተዳደሪያውን ደንብ (እስታቲስኮ) ሥርዓትና ደንብ ለማቋቋም መሠረታዊ ድንጋጌዎችና አሳቦች መትለም ወደ ቻለው ፤ የዳግማዊ ሡልጣን ሞሐመድ (፲፰፻፰ — ፲፰፻፴፱) አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ወደ ነበረበት ሁኔታ ተመልሰን ለማየት ስለምንፈልግ ነው ። እንዲሁም ደግሞ በ፲፯፻፰ ዓ. ም. ውስጥ የኢትዮጵያውያን ገዳም ማኅበር የተወሰዱበት አንዳንድ ንብረቶች ቢኖሩትም ስንኳ በነዚህ ንብረቶች ውስጥ የዴር ሥልጣን ገዳም ይገኝበት ነበር ማለትን ሊያሰማ አይችልም ። የሆነ ሆኖ በአማር ቃል ኪዳን አዋጅ መሠረት በኢየሩሳሌም ቅዱሳት መካናት ርስትነት ላይ ማንም ቢሆን ከግብርና ከሌላም አበል አከፋፈል ሁሉ ነፃ መሆኑ ይታወቃል ። በኢየሩሳሌም አገረ ገዢ እየሆኑ የተተኩትና እንዲሁም የኦትማን መንግሥት እንደራሴዎች የነበሩት ሁሉ ባወጡዋቸው ንጉሣዊ ትእዛዞችና ድንጋጌዎች በጠቅላላ ይህን የቃል ኪዳን አዋጅ ሳያከብሩና ሳይጠቅሱት እንዳላለፉ ይታወሳል ። ስለዚህ የኢትዮጵያውያን ገዳም የተጠየቀውን የመሬት ግብርና አበል ሳይከፍል በመቅረቱ በይዞታው ሥር የነበሩትን ርስትና ንብረት እንዲቀማ ሁኗል በማለት የኮፕት ማኅበር የሰጠው መግለጫ ታሪክን ሙሉ በሙሉ የሚቃወም ሁኖ ይገኛል ። እንዲሁም ደግሞ በተጨማሪ የኮፕት ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ በራሳቸው አነጋገር መስክረው እንደ ገለጹት ፤ የኢትዮጵያውያን ገዳም በኢየሩሳሌም አገር መካናት ቅዱሳት ውስጥ በርከት ያሉ ርስቶች እንደ ነበረው ካረጋገጡ ወዲህ እነዚሁኑ መልሶ እንዲያጣ የሆነበት ምክንያት የተናገሩት ስለሆነ ለዚህ አስረጂ የሚያቀርቡት ቢኖር በራሳቸው ኃያልነት ላይ የሚቀር ይሆናል ።



፮. የኮፕት ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ባቀረቡት ማስታወሻ ገጽ ፮ ፲ኛ ፓራግራፍ ላይ ፤ ብዙል ሂጂህ ፲፯- ፩ሺ፰፻፳፭ ሂጅራ ተጽፎ በወጣው ሰነድ ውስጥ የተመለከተውን ተቀብለውታል ። ይኸም ሰነድ የኢትዮጵያውያንን ገዳም ስም ለይቶ በመጥራት እንደሚገልጸው የሚከተለውን አብራርቶ ይጠቅሳል ። « በመካነ ቅዱስ መቃብሩ ቤተ ክርስቲያን በኩል አልፎ ያለው ገዳም በውስጡ ካሉት ክፍሎችና መኖሪያ ቤቶች እንዲሁም በላይኛው ቤተ መቅደስ ውስጥ የሚገኘውን ሁሉ ጨምሮ -----» ይላል ። ይህ ሕጋዊ ሰነድ የኢትዮጵያውያን ገዳም ማኅበር ለክርክሩ አስረጂ ብሎ ካቀረባቸው ሰነዶች ውስጥ አንዱ መሆኑ ነው ። ብፁዕነታቸው ይኸንን ሰነድ አብራርተው ለማስመስከር በመፈለጋቸው እጅግ ርቀው በመሔድ ሲገልጹ ፤ በዚህ ሰነድ አገላለጽ ገዳም ተብሎ የተጠራው ያሁኑ « አቡነ አብርሃም » ገዳም ነው በማለት ለዚሁም አስረጂ ይሆን ዘንድ አንዳንድ የንድፍ ምልክቶች እንዲቀርቡ አድርገዋል ። ይሁን እንጂ እነዚህ ሁሉ ምልክቶች በጂዎግራፊ አቀራረብ ረገድ ቢሆንም በቂ አስረጂ ናቸው ተብለው ሊቀርቡ ስለ ማይችሉ ይህን ለመረዳት ያህል ከተፈለገ በመካነ ቅዱስ መቃብሩ ቦታና ስለዚህም የተሰጠውን አገላለጽ በማመሳከር እቦታው ላይ ሁነው ከተመለከቱት ሊገኝ የሚችለው ውሳኔ የኢትዮጵያውያን ገዳም የተባለው ዴር ሥልጣን እንጂ ሌላ ሁኖ አይገኝም ። የላይኛው ቤተ መቅደስ የተባለውም አሁን የኮፕት ገዳም ከሚገኝበት ክልል ውስጥ የሚገኘው የአባ እንጦንዮስ ቤተ ክርስቲያን መሆኑ ነው ። ከዚህ በፊት ካቀረብናቸው ማስታወሻዎች ጋር ፎቶስታትክ ኮፒውን አባሪ አድርገን ወደ አቀረብነው የሡልጣን ሳሊም ንጉሣዊ ድንጋጌ እንደ ገና ወደ ኋላ በመመለስ የሚከተለውን ተጽፎ እናገኘዋለን ። « በስተደቡብ በኩል በቅዱስ መቃብሩ ቤተ ክርስቲያን የሚያገናኝ ሁኖ በሩ በስተደቡብ በኩል የሚከፈተው ታችኛው የኢትዮጵያውያን ቤተ መቅደስና በመካነ መቃብሩ ቤተ ክርስቲያን በር በኩል የሚገባው የዴር ሥልጣን ገዳም ከነቤቶቹና መኖሪያዎቹ ጭምር » ይላል ።

ስለዚህ በሁለቱም ሰነዶች ውስጥ ማለት በሡልጣን ሳሊም ንጉሣዊ ትእዛዝና እንዲሁም በ፩ሺ፰፻፳፭ በወጣው ሕጋዊ ሰነድ ውስጥ የተሰጠውን አገላለጽ እንደተመለከትነው ፍጹም አንድ ዓይነትና ተመሳሳይ ሁኖ እናገኘዋለን ። ሆኖም ንጉሣዊ ትእዛዙ « ዴር ሥልጣን » ብሎ የሚጠራውን ሕጋዊ ሰነድ ደግሞ «የኢትዮጵያውያን ገዳም» በማለት ይጠቅሰዋል ። ስለዚህ ዴር ሥልጣን የኢትዮጵያውያን ገዳም ማለት እንደሆነ ፍጹም የማያከራክር የመጨረሻው ውሳኔ እንደ መሆኑ በዚህ ምክንያት የኢትዮጵያውያን ገዳም ንብረት ሁኖ ይቀራል ። ከዚህ ቀጥለን እንደምንመለከተው የመተዳደሪያውን ደንብ ሥርዓት የሚወስነው ንጉሣዊ ትእዛዝ ከወጣ በኋላ ግን የኮፕት ማኅበር በዚህ ንብረት ያለ አግባብ ሲጠቀምበት ቆይቷል ። ኢትዮጵያውያን ገዳማቸውን ከግሪክ ኦርቶዶክስ ማኅበር እጅ አውጥተው መልሰው በይዞታቸው ለማድረግ እንደ ምን ቻሉ ?

www.ethiopianorthodox.org

፲፱/ እንዲሁም ለጥቅስና ለምስክር የጠቀስናቸውን መጻሕፍት እንደሚከተለው አያይዘን አቅርበናቸዋል ።

—የአሌክስ ጂባይን መጽሐፍ

—የዶር ሥልጣን ገዳም መጽሐፍ

--ጀርጊስ የሎታ የሎቲያስ አዋድ የጻፈው የዶር ሥልጣን መጽሐፍ

—እንዲሁም ከኮፕት ማኅበር የቀረቡትን ሰነዶች መልሰን ከዚህ ጋር በማያያዝ ለክቡርነትዎ አቅርበናል ።

## ው ሳ ኔ ።

በዚህ ክርክር ውስጥ የኢትዮጵያውያን መብት ግልጽ የሆነ ነው ። በዚህም ልክ የኮፕት ማኅበር ይህን መብት ለማጥፋት የሚያደርገው ጥፋት በግልጽ የሚታይ ነው ። ይህ ሲሆን የካቲት ፳፱ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ. ም. ተሰጥቶ የነበረው ውሳኔ ተመልሶ እንዲጸናና እንዲሠራበትም ለማድረግ ታላቅ ተስፋ እናደርጋለን ፤ ይህንንም የሚያሰኘን በተለይ ፩ኛ ይህ ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ ተብሎ የወጣ በመሆኑና ፪ኛም የኮፕት ማኅበር ባቀረበው አዲስ አስረጅ ውሳኔውን ለማገድ በቂ የሆነ ክርክር ይዞ ባለመቅረቡ ነው ። በተለይም ይህን ሁኔታ በመመልከትና በመገንዘብ የቅዱስ ሚካኤልና የአርባዕቱ እንስሳ ሁለት አብያተ ክርስቲያናት ለብዙ ምእመናን ዝግ ሁነው መገኘታቸው ትክክል ሕጋዊ መስሎ እንደማይታየን ለክቡርነትዎ ልናሳስብ እንወዳለን በተለይም እኛ የኢትዮጵያውያን መነኰሳትና ቀሳውስት ሥርዓተ ጸሎትና ቅዳሴ የምንፈጽምበት ሌላ የተለየ ቤተ ክርስቲያን የሌለን መሆናችንን ጭምር በማመልከት ነው ።

በነገሩ ትክክለኛ የሆነ ፍርድና ውሳኔ ለመስጠት ይቻልዎ ዘንድ በበኩላችን ልዑል እግዚአብሔርን የምንማልድ መሆናችንን በትሕትና እንገልጽልዎታለን ።

አባ ፊልጶስ
በሃሺሚታዊው የጆርዳን መንግሥት
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን
ሊቀ ጳጳስ ።

## የዳግማዊ ሡልጣን መሐመድ ንጉሣዊ ትእዛዝ ቊጥር ፫

ይህ ሰነድ ባቀረብናቸው ማመልከቻዎች ውስጥ ብዙውን ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል ፤ በተለይም የስታቲስኩዎ አስተዳደርን ሊመሠርት የቻለው ይህ ድንጋጌ መሆኑን አለመዘንጋት ነው ።

ከቱርክ ቋንቋ የተተረጐመ ።

በኢየሩሳሌም የሸሪዓ ጽ/ቤት

በቊጥር ፰/፪፻፺ ፈቃድ የተመዘገበ ።




www.ethiopianorthodox.org

ኋለሁ ፤ ይልና ገዳማቱን ሁሉ በዝርዝር ቆጥሮ በጌታችንና በእመቤታችን በዓላት ሁሉ ዘወትር በኔው ገንዘብ «መብራት» አብሩልኝ አታስታጉሉ የሌላን ገንዘብ ወይም መብራት አትጨምሩ ፤ እኔ በፍቅራችሁ ገመድ የተያዝኩ ነኝና ጸሎታችሁ ልመናችሁና በረከታችሁ ለዘለዓለሙ በኔ ላይ ይደር ፤ አሜን ፤

ታሪክ መርማሪዎች ምሥጢሩንና የዘመኑን የብርዕ ጽሕፈት አጣጣል ኃይለ ቃሉንም ትረዱ ዘንድ በግዕዝ ቋንቋ የተጻፈውን ደብዳቤ ፎቶ ኮፒውን ተመልከቱ ።


በስመ፡አብ፡ወወል
ድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡
አሐዱ፡አምላክ፡፡
በኵሉ፡ልብየ፡ዘኪያ
ለመልክ፡፡በኵሉ፡
ኀይልየ፡ወበኵሉ፡ነ
ፍስየ፡ወበኵሉ፡ሕሊ
ናየ፡ዘባቲ፡አስምክዋ
ዘእጉ ዝ፡በሕብለ፡አ
ምልኮ፡፡ በኢይትበ
ተክ፡ዘቦቱ፡አሐዱ፡
ለዝሉፉ፡ወኢይትኀ
ወክ
ተጽሕፈት፡ዛቲ፡መል
እክት፡ወከተ፡ዛቲ፡መ
ጽሐፈ፡ሲኖዶስ፡እም
ኀቤየ፡እምኀበ፡ዘርአ፡
ያዕቆብ፡

ንግሥተ፡ኢትዮጵያ፡
ኩ፡ውስተ፡ሀገረ፡
እንተ፡ትሰመይ፡ተጉለ
ቁራንየ፡ማኅበረ፡ቅዱ
ሳን፡እለ፡ይነብሩ፡ው
ስተ፡ኢየሩሳሌም፡ሀገ
ር፡ቅድስት፡በሰላመ፡እ
ግዚአብሔር፡አሜን፡፡
አስተበፅዓክሙ፡ፈድ
ፋደ፡፡ቀዳሚ፡አንክሙ፡
ኢውዋን፡ለቃለ፡ወንጌ
ል፡ዘይቤ፡ዘኢኀደገ፡
አባሁ፡ወእሞ፡ወብእ
ሲቶ፡ወውሉዶ፡ወገራ
ውሂሁ፡ወኵሉ፡ዘቦ፡፡

www.ethiopianorthodox.org



፫ኛ/ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ከደብረ ገነት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ በአፄ ዮሐንስ ሞት ተቋርጦ የጐደለውን ሥራ ፈጽመዋል ።

በተለይም ለገዳማቱ መርጃ የሚሆን ሁለት መቶ ሺህ ማርያ ትሬዛ ብር በገዳማቱ ስም ከባንክ አግብተው ዋናው ገንዘብ ለገዳማቱ ነዋሪ ሆኖ በወለዱ እንዲረዱበት አድርገው ሰጥተዋል ።

በተጨማሪም በደብረ ገነት ገዳም ውስጥ አንድ ትልቅ በኪራይ የሚያገለግል ቤት አሠርተው ሰጥተዋል ።

www.ethiopianorthodox.org



፬ኛ/ እቴጌ ጣይቱ ብጡል የዳግማዊ ምኒልክ ባለቤት ፤ በደብረ ገነት ገዳም ውስጥ አንድ ትልቅ የሚከራይ ቤት አሠርተው ከመስጠታቸውም በላይ ሌላ በኢየሩሳሌም ከተማ ሰፊ ቦታ ገዝተው ትልቅ የሚከራይ ቤት አሠርተው ሰጥተዋል ።

www.ethiopianorthodox.org



፷፯/ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ በኢየሩሳሌም ታላቅ ቤት አሠርተው ከኪራዩ ገቢ ገንዘብ ሲሶውን ገንዘብ ለገዳሙ መርጃ እንዲሆን ሰጥ ተዋል ።

www.ethiopianorthodox.org



፺ኛ/ ግርማዊት እቴጌ መነን ፤ በዮርዳኖስ ገዳም ቦታ ገዝተው አንድ ዘመናዊ ሥራ የሆነ ቤተ ክርስቲያን አሠርተው በቅድስት ሥላሴ ስም አስቀድሰው ለማኅበሩ ከማስረከባቸውም በላይ ለቤተ ክርስቲያኑ ሕንፃ መጠባበቂያና ለማኅበሩ መርጃ የሚሆን በአዲስ አበባ በሁለት መቶ ሠላሳ ሺህ ብር ( ፪፻፴ሺህ ብር ) ፎቁ የስድስት ቤተሰብ መኖሪያ የሆን የምድር ቤቱን ሱቅ አድርገው ታላቅ ሕንፃ አሠር [illegible] ዳኖስ) በሚል ስያሜ ለኢየሩሳሌም ገዳማት ማኅበር ሰጥተዋል ፡፡

www.ethiopianorthodox.org



የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ባለቤት ደን ግርማዊት እቴጌ መነን ከቅዱሳት መካናት አንዱ ከሆነው በገዳመ ዮርዳኖስ ለኢትዮጵያ ማኅበር ቤተ ክርስቲያኑንና ቤተ ማኅበሩን ባንድነት አያይዘው ያሠሩት ታላቁ የኢትዮጵያ ገዳመ ዮርዳኖስን ሕንፃ የሚያሳይ ሥዕል ።

የግል ቤተ መጻሕፍት

www.ethiopianorthodox.org



፺ኛ/ ክቡር አፈ ንጉሥ ነሲቡና ባለቤታቸው ወይዘሮ ደስታ ደኅና ቦታና ቤት ገዝተው ለገዳሙ ሰጥተዋል ፤ በኋላም ባለቤታቸው ክብርት ወይዘሮ ደስታ ከባላቸው ሞት በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ሔደው ሲኖሩ በትርፉ ቦታ ላይ ትልቅ ቤት ተጨማሪ ሠርተው ሁሉንም ለገዳሙ ሰጥተዋል ።

www.ethiopianorthodox.org



ክብርት ወይዘሮ (እማሆይ) ደስታ የአፈ ንጉሥ
ነሲቡ ባለቤት በኢየሩሳሌም ።

www.ethiopianorthodox.org



፷፰ኛ/ ክቡር ደጃዝማች ባልቻ አባ ነፍሶ ፤ በኢየሩሳሌም አንድ ቤት እን ደተሠራ ገዝተው ለኢየሩሳሌም ገዳም ሰጥተዋል ።

www.ethiopianorthodox.org



፱ነኛ/ ክብርት ወይዘሮ አማረች ዋለሉ ፤ ዓለምን መንነው (ንቀው) ወደ ኢየሩሳሌም ሔደው ሲኖሩ በኢያሪኮ ከተማ አንድ ሰፊ ርስት ከነቤቱ ሰጥተዋል ፤ በኢየሩሳሌም ከተማም አንድ ይኖሩበት የነበረውን ቤት ርስት አድርገው ለኢትዮጵያ ገዳም አውርሰው በኢየሩሳሌም አርፈዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

፲ኛ/ ክቡር ራስ ወልዴ አንድ አነስ ያለች ቦታ ገዝተው ቤት አሠርተው ሰጥተዋል ፤ ለማኅበሩ በጸሎት ደብዳቤም አባቶቹ ወልዴ ለኢየሩሳሌም ገዳም ርስት ሰጠ ሲባል ለሌሎች መልካም አርአያ መሆኑን እንጂ የማነሱን አትመልከቱ ብለው የጸሎት ቃል ማኅበሩን ደስ አሰኝቷል ።

፲፩ኛ/ ልዑል ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴና ባለቤታቸው ልዕልት ወይዘሮ ጽጌ በኢያሪኮ ከገዳሙ ቦታ ላይ ቤት አሠርተው ሰጥተዋል ።

፲፪ኛ/ ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ የኢሉባቦር ጠቅላይ ግዛት ሊቀ ጳጳስ በፈቃዳቸው ሀገረ ስብከታቸውን ትተው ወደ ኢየሩሳሌም ሔደው በኢትዮጵያ ገዳም ሲኖሩ ፥ ኢያሪኮ በገዳሙ ቦታ ላይ የሠሩትን ቤት ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ለገዳሙ ሰጥተዋል ።

፲፫ኛ/ ወይዘሮ አልታዩ ወርቅ የክቡር ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ባለቤት በደብረ ገነት ገዳም ውስጥ ፎቅና ምድር ቤት ያለው ጥሩ ቤት አሠርተው ሰጥተዋል ።

፲፬ኛ/ ወይዘሮ በየነች ገብሬ የሐረሩ የደጃዝማች ገብሬ ልጅ ባላቸው ከውጋዴ ዘመቻ መንነው እንደታጡ እርሳቸውም ኢየሩሳሌም ድረስ ሔደው በዮርዳኖስ በረሃ መንነው ሲኖሩ ፤ አንድ አነስተኛ ቦታ ገዝተው ቤት ሠርተው ለገዳሙ ሰጥተው ፤ በዮርዳኖስ አርፈዋል ።

፲፭ኛ/ አቶ ይልማ ወልደ ገብርኤል በደብረ ገነት ገዳም ውስጥ የእንግዳ መቀበያ የምትሆን አንድ አነስተኛ ሳሎን አሠርተዋል ።

መምህር ወልደ ሰማዕት በዘመናቸው በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያን ገዳም ለማስፋፋት ብዙ ጥረት ያደረጉ ታላቅ ባለውለታ መምህር ናቸው ። የድካማቸውንም ውጤት በሥፍራው ተገኝቼ በተረዳሁት መጠን ከብዙ በከፊል (በጥቂቱ) እንደሚከተለው እገልጻለሁ ።

መምህር ወልደ ሰማዕት የትውልድ አገራቸው ኢትዮጵያዊ በተለይም በሸዋ ጠቅላይ ግዛት ቡልጋ ከሚባለው ወረዳ የተወለዱ ሰው ናቸው ።

ከአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ቀደም ብለው በምንኵስና ሕግ መንነው በሀገር ቅድስት ኢየሩሳሌም በኢትዮጵያ ገዳም ይኖሩ ነበር ።

አፄ ዮሐንስ እንደነገሡም በኢየሩሳሌም ገዳማት ማኅበር በገዳሙ ሥርዓት (ሕግ) ተመርጠው በኢየሩሳሌም ለኢትዮጵያ ገዳም ማኅበር አበምኔት (መምህር) ሆነው በማኅበሩ ምርጫ ተሾሙ ።

www.ethiopianorthodox.org

